# ታጠቅ

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

የቲዎሪ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## የብሔሮች ጉዳይ

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፡
P.O.BOX 3198
10364 STOCKHOLM3
SWEDEN

ቁጥር፡ 1
መስከረም - የካቲት 1965

# መቅድም

በ1960ዎቹ መጀመርይ ላይ በኢትዮጵያ ተማሪዎች በአጠቃላይና በተለይም በአዉሮፓና በሰሜን አሜርካ በሚገኙ የተማሪው ማህበራት ውስጥ ሰፋ ያለ ግዜ ተሰጥቶ ውይይት ከተደረገባቸው ጉዳዮች ውሰጥ አንዱና ዋነኛው የብሄሮች ጥያቄ ነበር። ገና ከጅምሩ የዛሬይቱን ኢትዮጵያን ምስረታ ታሪክ በመረዳት፤ ኢትዮጵያ በሚለው ግዛት ውስጥ በጠብመንጃ ሀይል ተገደው የተጠቃለሉ ህዝቦች ከዚህ የብሄሮች እስር ቤት ለመላቀቅ የጀመሩትን የነጻነት ትግል በሚመለከት የተነሳውን የአስተሳሰብ ልዩነት መሰመር ለማስያዝ የተማሪው ማህበራት ካደረጉት ጥረቶች አንዱ ትምህርታዊ የጥናት ጽሁፎችን ማዘጋጀትና በዝህም ላይ ውይይት ማድረግ ነበር።

"ታጠቅ  ቁጥር 1" መጽሄት "የብሄሮች ጉዳይ" በሚል ርእስ ይዞት የወጣው ጽሁፍ  ከታተመ እነሆ ግማሽ ምዕተ ዐመት ሊሞላ ጥቂት ወራት ብቻ ቀርተዋል፡፡ መጽሄቱ ከታተመ ወዲህ ኢትዮጵያ ከፊውዳላዊ ስርዓት ተላቃ፣ በወታደራዊ አስተታደር አርጋ ሶሻልዝምን ሞክራ፣ ወደ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ተሸጋግራ፣ እሱንም ጥላ አሁን ምኑም የማይታውቅ ስርዓት ውስጥ ብትገኝም እነሆ ዛሬም ከመነሻው የተጠናወታትና መጽሄቱ አርስት ያደረገው የብሄሮች ጉዳይ ዛሬም እልባት አላገኘም።

መጽሄቱ በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1965 ማለትም በፈረንጆቹ 1973 ዓ/ም ሲታተም በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ውጪ በይፋ የተቋቋመና እራሱን ይፋ ያደረገ አንድም የፖለቲካ ድርጅት አልነበረም። የፖለቲካ ድርጅት በሌሌበት ሁኔታ ውስጥ ነው እንግዲህ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በራሱ ላይ ወስኖ ይህንን እጅግ የተወሳሰበ የብሄሮችን ጥያቄ ለመተንተን የተነሳው። ጽሁፉ በተለይ ያነጣጠረው በጊዜው በውጭ አገር በሚኖሩ የኢትዮጵያ ተማሪያዎች መካከል በብሄሮች ጥያቄ ላይ ተከስቶ በነበረው አለመግባባት ላይ ይሁን እንጂ መሰረታዊውን በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ብሄሮችን ግንኙነትም የዳሰሰ ነው።

ከላይ እንዳልነው ይህን ጽሁፍ ያዘጋጀው በአውሮፓ የኢትዮጲያ ተማሪዎች ማህበር ነው። ይህም ማህበር ከጥቂት ዐመታት በኋላ ራሱን ይፋ ካደረገው መኢሶን ጋር የነበረው ትስስር ለሁሉም ግልጽ ነው። ጽሁፉ "ንጋቱ አምዴ" በሚል የብዕር ስም ይውጣ እንጂ የዚህ ጽሁፍ ዋና አዘጋጆች በወቅቱ ማህበሩን ከፊትም ሆነ ከኋላ ሆነው ሲያንቀሳቅሱ የነበሩትና በኋላም በመኢሶን መሪነት የምናውቃቸው ሃይሌ ፊዳ፣ ነገደ ጎበዜ፣ ከበደ መንገሻ፣ አንዳርጋቸው አሰግድ ወይም ከሌሎች ጓዶቻቸው ውስጥ እንደሚሆን መገመት ይቻላል። የጽሁፉ ብቸኛ ጸሃፊ እገሌ ነው ባንልም ፣ በዚህ ጽሁፍ ዝግጅት የሃይሌ ፊዳ ሚና ከፍተኛ እንደሆነ መገመትና፣ አቋሙም በእጅጉ የተንፀባረቀበት መሆኑን በመህበሩ ውስጥ ከነበረው ሚናና በብሄረሰቦች ጥያቄ ላይ ከነበረው የማያወላውል አቋም ተነስተን መናገር እንችላለን። በዚህ አጋጣሚም ሃይሌ ፊዳ በብሄረሰቦች ጥያቄ ላይ ያለውን አቋም ለራሳቸው አቋም እንዲረዳ አጣመው ለማቅረብ ለሚፈልጉና የህይወት ታሪኩን እንጽፋለን በሚል ሽፋን አቋሙን አለሳልሰው ለትምክህተኛው እንዲዋጥ (sanitize) አድርገው ለሚያቀርቡት ይህ ጽሁፍ ትክክለኛውን አቋሙን ለማሳየት ይጠቅማል ብለን እናስባለን።

ይህ ጽሁፍ እንደገና እንዲታተምና አንባቢ እጅ እንዲገባ የፈለግነው በተለያየ ምክንያት ነው። አንደኛ በታርካዊነቱ። ጽሁፉ በተማሪ እንቅስቃሴ ውስጥ የተነሳውን ክፍፍል ሰፋ ባለ ሁኔታ ከማሳየትም አልፎ የልዩነቶቹን አመጣጥና መሰረት በሰፊው ስለሚተነትን ወደኋላ መለስ ብለው የኢትዮጵያ ተራማጆችን ታሪክና የብሄረሰቦች ጥያቄ ላይ ምርምር ለሚያደርጉ ሁሉ ጠቃሚነቱ እጅግ ከፍ ያለ በመሆኑ፣ ሁለተኛ ዛሬ በተወሰኑ ክፍሎች በኢትዮጵያ እየታየ ያለውን የብሄሮችን አለመግባባትና ቅራኔ ትላንት የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት የፈጠረው አድርጎ የሚወስድ ሰፊ የህብረተሰብ ክፍል ስላለ ይህንን የተሳሳተ አስተሳሰብ ለማረም ይረዳል ብለን ስላሰብን፣ ሶስተኛና ዋነኛው ምክንያት ደግሞ ጽሁፉ ከታተመ ሃምሳ ዓመታት ያህል ቢቆጠሩም ዛሬም ላለንበት ሁኔታም ጽሁፉ እጅግ ግዜያዊ (relevant) መሆኑን ስላመንበት ነው።

ከላይ እንደገለጽነው የህ ጽሁፍ ከተጻፈበት ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያ ብዙ ለውጥ አስተናግዳለች...ይሁን እንጂ በዚህ ጽሁፉ ውስጥ የተነሱ ጉዳዮች እልባት አላገኙም....ዛሬም ኢትዮጵያ የብሄሮች እስር ቤት መሆንዋ አላበቃም....ያኔ ከጅምሩ የጽሁፉ አዘጋጆች "በኢትዮጵያ ውስጥ አማራ ያልሆኑት ብሔሮች ላይ የሚደረገው ጭቆና ፈጽሞ መስመርና ልክ የሳተ በመሆኑ ትንሿ ....... እንኳን ብትሆን ትልቅ ቃጠሎ ልታስነሳ"" ትችላለች ብለው የሰጠው ምክርና .. የአማራን ብሄር ምሁራን ""ኢትዮጵያ ማለት እኔ ብቻ ነኝ" ብሎ ካከተመው ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜት ለአንዲት ሰከንድ እንኳን ጨርሶ ባልተቆራረጠ አንደበቱ፣ ለአንዲት ሴኮንድ እንኳን ባልተፍታታ ህሊናው .......ስለአንድነት ለመስበክ መብት የለውም፡፡" ብለው ያስጠነቀቁት ያለምክንያት አልነበረም ... የዛሬው ሰቆቃ ታይቶአቸው እንጂ። የሚያሳዝነው ይህን የመሰለ ደፋር፣ እውነቱን ፊት ለፊት የሚጋፈጥና በህዝቦች መሃከል ሊፈጠር ለሚችለው የትግል አንድነት አቅጣጫ የሚቀይስ ጽሁፍና የያዛቸው ቁም ነገሮች ለብዙ አመታት ተደብቆና ደዋ በልቶት መኖሩ ነው። ለዚህ ብዙ ምክንያት ቢኖርም በዋናነት ግን ሃይሌ ፊዳና ጓዶቹ ከሞቱ በኋላ እነሱ የፈሩት የአማራ ትምክህተኝነት በግራ ሃይሎች ውስጥ ማየሉና እንዲሁም ይህን የእነሱን አቋም በድፍረት ይዞ የሚቀጥል ሀይል በድርጅቱ ውስጥ መጥፋቱ መሆኑን እንገምታለን። መልካም ንባብ።

ታህሳስ 2014 (February 2022)

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ በሚገኝበት ልዩ ሁኔታና ጊዜ ምክንያት “ከአቅሙ በላይ የሆኑ” እውን ጥያቄዎችን እያነሳ መልሳቸውን ከሞላ ጎደል ሰጥቷል፡፡ ከነዚህ ጥያቄዎች አንዳንዶችን ለመጥቀስ ያህል ”መሰረታዊ ለውጥ”፡ “የብሔሮች ጥያቄ”፡ “በኢትዮጵያ የሚደረገው አብዮት አይነትና ጠባይ” … ወዘተ. የመሳሰሉት ናቸው፡፡

እነዚህን ሁሉ አርእስቶች ትክክለኛ መልሳቸውንና ገባራዊ መፍትሄያቸውን ማግኘት የነበረባቸው በአብዮታዊ የፖለቲካ ፓርቲ አማካኝነት ነበር፡፡ ነገር ግን ይህን አይነት ድርጅት በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ገና ብቅ ስላላለ የተማሪ እንቅስቃሴያችን ኃላፊነቱን እንዲወሰድ ሁኔታው አስገድዶታል፡፡

ለምሳሌ ጊዜያዊ በነበረው በብሔሮች ጥያቄ ላይ ከብዙ ጥናት ውይይትና ክርክር በኋላ እውነተኛ የሆነ አቋም ለመውሰድ ችሏል፡፡ ይህም ውሳኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚካሄዱት ብሔራዊ ትግሎችና ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የመጀመሪያ ደረጃ እድገት ጥሩ ድጋፍ ሆኖአል፡፡ ጉባኤው ያሳለፈው ውሳኔና ያስከተለው ውጤት እሰይ የሚያሰኝ ነው፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ ከመጀመሪያው ግብ ደርሷል በመባል ባለበት መቆም የለበትም፡፡ በነሐሴ 1963 ዓ.ም በርሊን ከተማ ውስጥ የተሰበሰበው 11ኛው በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማሕበር ጠቅላላ ጉባኤ ካሳለፋቸው ውሳኔዎች አንዱ ስለብሔር ጉዳይ በየቅርንጫፍ ማሕበራት ውስጥ ውይይት እንዲቀጥልና መጽሔቶቻችንም በዚሁ አርእስት ትምህርታዊ የሆኑ ትንታኔዎችን እንዲያቀርቡ የሚያሳስብ ነበር፡፡

ከዚህ ሌላ በዚሁ ዓ.ም በአሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማሕበር 19ኛ ጉባኤ ስለብሔሮች ጥያቄ በወሰደው ትክክለኛ አቋም ባለመስማማት አንዳንድ አባሎች የነበሩ ጓዶች ከማህበሩ መውጣታቸው ይታወሳል፡፡ ያውሮፓዉና የአሜሪካው ማሕበራት ያሳለፉትን ሳይንሳዊ ዉሳኔ በመጻረር እስካሁን ድረስ ስህተታቸውን ለማረምና ከማሕበሩ ጋር ያላቸውን ቅራኔ በውስጥ ማሕበር ዲሞክራሲ በመጠቀም ለመፍታት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡

የስህተታቸው ምንጭ አውቀው ሆነ ሳያውቁ ከተነከሩበት ከገዥው መደብ ርእዮተ አለም የፈለቀ ነው፡፡ "መሬት ተቆረሰ"፤ "ባህር መውጫ ጠፉ"፤ ይላሉ የባለጉልት ከበርቴ /ፊውዶ ቡርዣ ስርአት ወኪሎች፡፡ ስለዚህ በአንድነት ስም ህዝቡ ጨፍጭፉ ይላሉ፡፡ መሬቱ ገንዘቡ እንጂ ሰው አይታያቸውም፡፡ የተቃዋሚዎች ጓዶች እርስ በእርሱ የሚቃረን አቋም ደግሞ በቀላል አቋም ቢገለጥ፤ ስለነጻነት እየተናገሩ ነጻነት የሚገኝበትን መንገድ እንደመዝጋት የሚቆጠር ነው፡፡ በሌላ አነጋገር የወደፊቱን ከፍተኛ አንድነት እንደግፋለን ካሉ በኋላ የአሁኑ የጭቆና አንድነት መፍረስ እንደሚያስፈልገው ሲነገር አካኪ ዘራፍ ይላሉ፡፡ አልሸሹም ዞር አሉ ነው፡፡ በብሔሮች ጥያቄ ላይ የገዥው መደብና የተቃዋሚዎች ጓዶች ልዩነት ያነጋገር ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ወደዱም ጠሉም እንዋጋለን የሚሉትን ስርአተ መንግስት በተገላቢጦሽ ያገለግሉታል ማለት ነው።

ከላይ የተገለጡትን ምክንያቶች በመመርኮዝ በዚህ የታጠቅ ቁጥር ውስጥ ስለብሔሮች ጉዳይ በሰፊው የሚያብራራ ሃተታ ቀርቦአል፡፡ የጽሁፍ አላማ በመጀመሪያ ትምሕርታዊ መልዕክት ለማስተላለፍ ሲሆን ቀጥሎ ደግሞ የማሕበራችንን አቋም የሚቃወሙትን ጓዶች መሰረታዊ ስህተት በማሳየት አቅጣጫቸውን እንዲለውጡ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ሀተታው ስለብሔሮች ጉዳይ

ተግባብተናል በማለተ ብቻ የሚታለፍ የመጨረሻ ቃል መሆን የለበትም።
አንባቢዎች አስተያየታችሁን፤ ትችታችሁንና ጥያቄያችሁን በትንተና ወይም
በደብዳቤ መልክ ብታቀርቡልን ጥሩ የሀሳብ መለዋወጥ ሊያስከትል ይችላል፡፡

**ታጠቅ**

# <u>የብሔሮች ጉዳይ በኢትዮጵያ</u>

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ከተውተበተበበት ጭቆና ተላቅቆ በሰላምና በነጻነት የሚኖርበት አዲስ ኑሮ ይጠይቃል፡፡ በሃብታምና በለምለም አገር ላቡን አንጠፍጥፎ የሚኖር ሕዝብ ከረሃብ፤ ከድህነት፤ ከበሽታና ከድንቁርና ጨርሶ የተፍታታ ኑሮ ቢጠይቅ ይገባዋል፡፡ መብቱም ነው፡፡

ኢትዮጵያ ሀብታም ነች፡፡ ሕዝቡ ታታሪ ነው፡፡ ኑሮው የተጎሳቆለ ቢሆን፤ ሕዝቡ በሙሉ ታጥቆ የሚባክነው ለጥቂት ቱሃኖች የተትረፈረፈ ኑሮ ለማቅረብ ስለሆነ ብቻ ነው፡፡ ጥቂት ሰዎች የሃገሪቱን መሬት በሰሞን፤ በጉልት፤ በርስተጉልት.... ስም የግል ሀብታቸው አድርገው ይዘውታል፡፡ እነዚህ ጥቂት ሰዎች የሀገሩን ሕዝብ በሙሉ በተገዥነት እጅና እግሩን ጠፍረው አስረውታል፡፡ ጉልበቱን ይበዘብዙታል፡፡ ይህም ማለት የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብትና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ጉልበት በመቶ ለሚቆጠሩ ሰዎች ጥቅም እንዲውል ተደርጓል ማለት ነው፡፡ ባጭሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትከሻ ላይ የጠነባ የፊውዳሊዝም ቀንበር ተጭኗል፡፡

ነገር ግን የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደቱሀን የሚመጠው ይህ የጉልተኛ ስርአት ዛሬ ብቻውን አይደለም፡፡ ከጥቂት ዘመናት ወዲህ የባእዱ ጭቆና ቀንበር በሃገሪቱ ላይ ጥላውን ዘርግቶ እናየዋለን፡፡ እነዚህ ባእዳን ከበርቴዎች ከሃገሪቱ በዝባዦች ጋር በመሻረክና ከነርሱም ጋር በመደጋገፍ ኢትዮጵያን የጥሬ እቃ ምንጭ፤ የፋብሪካ እቃ ማራገፊያ የሀብታቸው ማፍሪያና የጦራቸው ማስፈርያ አድርገዋታል፡፡ ይህም ማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ የተፈጥሮ ሀብት ለባዕዳን ጥቅም መዋል ጀምሯል ማለት ነው፡፡ የሀገራችን እንዱስትሪና ፋብሪካ በሀገሬው ነጋዴና ታታሪ ሰው እንዳይካሄድና እንዳይበለጽግ መንግስቱ የሚያግዛቸው ባእዳን አስቸግረውታል

ማለት ነው፡፡ ባጭሩ በኢትዮጵያ ሕዝብ ትከሻ የኢምፔሪያሊዝም በተለይ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም/ ቀንበር ተጭኗል ማለት ነው፡፡

በኢትዮጵያ ምንም አይነት ደህንነት ሊመጣ የሚችለው ፊውዳሊዝምና ኢምፔርያሊዝም በሕዝብ አመጽ ተደምስሰው በእነሱ መቃብር ላይ አዲስ ዲሞክራሲያዊ ስርአት ሲመሰረት ብቻ ነው፡፡

አላማው ይህ ሲሆን ለተፈለገው ሕዝባዊ ድል በኢትዮጵያ የሚገኙ የፊውዳሊዝምንና የኢምፔሪያሊዝምን ጭቆና የሚቃወሙ ኃይሎች ሁሉ በአንድነት ተሰልፈው መታገል አለባቸው ፡፡ ተራማጆች በሙሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ለዚህ አላማ ሊረዱ የሚችሉትን ሃይሎች በጥሞና በማጥናት ትግላቸውን መሰብሰብና ማደራጀት አለባቸው፡፡ ይህንንም በምናደርግበት ጊዜ "በኢትዮጵያ የፊውዳሊዝም ጭቆና አለ፣ የኢምፔሪያሊዝም ጭቆና አለ" ብሎ መዝጋት ብቻ አይበቃም፡፡ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በዘመኑ የታወቁት የጭቆና አይነቶች በሙሉ በቀድሞ መልካቸውም ሆነ በአዲስ ጥበብም የተጠራቀሙበትና የሰፈሩበት የጨለማ አገር ናት፡፡ ከነዚህም ጭቆናዎች ውስጥ በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም ላይ በመደረብ በአንዳንድ ብሔሮች ላይ የተጫነው ዋናው የብሔሮች ጭቆና ነው፡፡

ዛሬ በኢትዮጵያ በርግጥ የብሔሮች ጭቆና አለ፡፡ እንዲያውም ዛሬ በኢትዮጵያ ይህ የብሔሮች ጉዳይ በጣም አጣዳፊና የጋለ ጉዳይ ነው ብለን እናምናለን፡፡ የገዥው መደብ ይህ ጉዳይ ቢድበሰብስለት ይወዳል፡፡ እንዲያውም ቢነሳበት አይወድም፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ውስጥ አማራ ያልሆኑት ብሔሮች ላይ የሚደረገው ጭቆና ፈጽሞ መስመርና ልክ የሳተ በመሆኑ ትንሿ እንኳን ብትሆን ትልቅ ቃጠሎ ልታስነሳ ስለምትችል ነው፡፡

በዚህ ጊዜ ታዲያ የተራማጆች አቋም ምን መሆን አለበት፡፡ በአንድ በኩል ተራማጆች ነን እያልን በሌላው በኩል ደግሞ እንደገዥው መደብ ይህን ታሪክ የወለደውን የብሔሮች እንቅስቃሴ ማድበስበስ ነው? ወይስ በሃገሪቱ ዛሬ የብሔሮች ጭቆና አለ፤ ይህም ትክክለኛ የሆነ የብሔሮች እንቅስቃሴ አስከትሏል በማለት ተገቢ ድጋፍ መስጠት? "ዋናው የመደብ ትግል ነው"፤ "የብሔሮች ንቅናቄ የትግል አንድነትን ያደፈርሳል"፡ የትግል አንድነትን ያፈርሳል እያሉ በሕዝብ ትግል ማላገጥ ነው ወይስ ይህን ትክክለኛ ትግል ተቀብሎ በተቻለ ለኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ <u>በሙሉ</u> እውነተኛ ነጻነትና እውነተኛ አንድነት እንዲውል ተገቢውን መስመር ማስያዝ፡፡

በዚህ ጉዳይ ከጥቂት ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ልዩነት መፈጠሩን ሁሉም ያውቃል፡፡ በአውሮፓው 11ኛ ጉባኤና በአሜሪካው 19ነኛው ጉባኤ ላይ የተወሰዱትን ትክክለኛ አቋሞች በመቃወም አንዳንድ ጓዶች ከኛ የተለየ አቋም ወስደዋል፡፡ እነዚህ ጓዶች በኢትዮጵያ የሚታዩትን ብሔራዊ ንቅናቄዎች ለማቃለልና አብዮታዊ ይዘታቸውን ለማሳነስ የሚችል የተሳሳተ ፖለቲካ ሲከተሉ ይታያሉ፡፡ ከነዚህ ጓዶች ጋር ስለብሔራዊ ንቅናቄዎች ታሪካዊ አመጣጥ፤ ስለአብዮታዊ ይዘታቸው ከመደብ ትግል ጋር ስላላቸው ግንኙነት ስለትግል አንድነት ጉዳይና በመጨረሻም ብሔሮች የገዛ እድላቸውን ለመወሰን ስላላቸው መብት ጉዳይ የተለየ አስተሳሰብ እንከተላለን፡፡

በነዚህ መስመሮች ቀስ በቀስ የሚጠራቀሙት ልዩነቶች መጨረሻ ላይ ሁለቱ ልዩ ልዩ ጐዳናዎችን ያስይዙናል፡፡ እኛ የመረጥነው ጎዳና ዛሬ ለሚፈለገው ትግል ተግባራችንን አጣርቶ የሚያሳይና ለረዥሙ ትግላችን ብርሃን የሚሰጥ የሰፊውን ሕዝብ አንድነት ከብረት የሚያጠነክር ወደአብዮታዊ ድል የሚመራ አቋም ነው፡፡ የተቃዋሚ ጓዶች "ቴዮሪ" ግን የጊዜውን ዋና ተግባር በሚገባ አያሳይም፡፡

የጊዜውን ዋና ጠላት በሚገባ አይዋጋም፡፡ ስለዚህም በተራማጅነት የቀረበ አቋም ቢሆንም ቅሉ የትምክህተኛውና የጊዜውን ትግል የሚሸሸው ሁሉ መሸሸጊያ ዋሻ እንጂ ምንም አይነት የትግል መሳሪያ ነው ሊባል አይችልም፡፡

ሀ/ <u>የብሔሮች ንቅናቄ የጊዜው የኢትዮጵያና የአለም ሁኔታ የፈጠረው ትክክለኛ ንቅናቄ ነው፡፡</u>

ብዙውን ጊዜ በኢትዮጵያ “ስለብሔራዊ ስሜት” ብዙ ሰዎች “ኢትዮጵያዊነት” ወይም “የኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት” ብለው የሚጠሩት የአማራውን ብሔራዊ ስሜት ብቻ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ከተሜው ንዑስ ከበርቴ አማራ ኢትዮጵያዊነትና አማራነት ፈጽሞ ተደበላልቀውበታል፡፡

እርግጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢምፔሪያሊስቶች መናቁና መገፋቱ አንገብግቦት በሃገር ፍቅረ መንፈስ የተነሳሳ ብሔራዊ ስሜት ብቅ ብቅ ማለት ጀምሯል፡፡ አማራው ከኢምፔሪያሊስቶች የሚመጣውን መራራና አጥፊ ተንኮል ለመቋቋም ባህሉን ከፍ ለማድረግና ለማበልፀግ፤ ማንነቱን ለማሳወቅ ከወረሰው ታሪኩ መልካም መልካሙን እየቀሰመ ወደፊት ለመራመድ መሞከሩ ግሩም ነው፡፡ ይህ የሃገር ፍቅር ስሜት ከኢምፔሪያሊስቶች ነጻ የሆነች አገር ለመመስረት ታላቅ የትግል ሞተር ይሆናል፡፡ ይህ ጭቆናን የሚቃወም ትክክለኛ ብሔራዊ ስሜት ነው፡፡

ነገር ግን በገዥው መደብ ቁንጮዎች የተነዛ በኢትዮጵያ ያሉትን ሌሎች ብሔሮች የሚንቅና የሚያንቋሽሽ የአማራውን ባሕል የበላይነት የሚሰብክ አድሃሪ የሆነ ብሔራዊ ስሜት አለ፡፡ ይህ አድሃሪና ከሌሎች በላይ ነኝ የሚል ስሜት ስለሆነ ትምክህተኛ /ሾቪንስት/ ብሔራዊ ስሜት እንለዋለን፡፡ እንዲህ አይነቱ አማራነትንና ኢትዮጵያዊነትን ፈጽሞ የሚያደበላልቅ የኢትዮጵያን የሃገር ልብስ “ልልበስ”

ያለእንደሆን የሚያጠልቀው የአማራውን ሽማና እጀ ጠባብ ነው፡፡ የኢትዮጵያን የሀገር ዘፈን ልስማ ያለ እንደሆን አምባሰልና ትዝታ ናቸው ትዝ የሚሉት፡፡ የኢትዮጵያን የሃገር ምግብ ልብላ ሲል ጤፍ እንጀራ፤ ዶሮ ወጥ፤ ምንቸት አብሽ ናቸው ሽው የሚሉበት፡፡ የሃገር ባሕል ይጠበቅ ሲል የጀግናውን የአበሻ ክርስቲያን ባሕል ለማስከበር መነሳቱ ነው፡፡ በዚህ መልክ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ኢትዮጵያዊነትና አማራነትን የሚያማቱ ሁሉ በልዩ ልዩ ባሕሎች ቋንቋዎች ሃይማኖቶች በተዥጐረጐረችው ኢትዮጵያ ለመላ ተበዝባዦች ነጻነት አንድነትና እድገት ለሚደረገው የጋራ ትግል ፈጽሞ አደገኛ ናቸው፡፡

ዛሬ በኢትዮጵያ በዚህ የአማራ የበላይነት ብሔራዊ ስሜት በመመራት "ኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ታሪክ ያለው፤ አንድ ባሕል ያለው፤ በአንድ አይነት ብሔራዊ ስሜት የተሳሰረ ነው" እያሉ በየአቅጣጫው የተሰበጣጠረውን የሃገሪቱን ሁኔታ የሚክዱ ሁሉ የኢትዮጵያን ተበዝባዦች እውነተኛ ነጻነትና አንድነት ጠላቶች ናቸው፡፡

መታወቅ ያለበት አንድ ግልጽ ነገር አለ፡፡ በኢትዮጵያ ከአማርኛ ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ከሀበሻው ታሪክ ሌላ የራሳችው ታሪክ ያላቸው ከክርስትና ሃይማኖት ሌላ የተለየ ሃይማኖት የተቀበሉ ከደገኛው ሀበሻ ስልጣኔ ሌላ የራሳቸው ስልጣኔ የሚያኮራቸው ሌሎች ብሔሮች አሉ፡፡ ከነዚህም ብዙዎቹ ከመቶ አመታት ወዲህ ተወርረው በሃይል የተያዙና አሁንም በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በጦር ሃይል ታስረው የሚገኙ ናቸው፡፡ እነዚህ ብሔሮች በተያዙበትም ወቅት ሆነ አሁንም እጅግ ከፍ ያለ ግፍና ውርደት የሚደርስባቸው ናቸው፡፡ ግን እነዚህን እውነቶች መቀበል ብቻውን ብዙ ዋጋ የለውም፡፡ እርግጥ ነው እነዚህን እውነቶች መቀበል የግዜው ስርአት የሚነዛቸውን አንዳንድ አስካሪ ፕሮፕጋንዳዎች ወዲያውኑ ፉርሽ ያደርጋቸዋል፡፡ ለምሳሌ ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ግማሹ ያህል በክርስትና አያምንም፡፡ ይህ ሲታወቅ

ኢትዮጵያን የክርስቲያን ደሴት የሚያደርጋት ቅጥ ያጣ ፈሊጥ ክርስቲያን ያልሆኑትን ኢትዮጵያውያን ጨርሶ እንደሌሉ እየቆጠረ የሚያዋርዳቸው በድብቅ ነው፡፡ በዚህ መልክ የአበሻውን ክርስቲያን ስልጣኔ ያላዋሃዱ በንጉሰ ነገስት ግዛት ውስጥ የሚኖሩ ብሔሮች ሌላ መአት አይነት ጭቆናና ውርደት አለባቸው፡፡

ኢትዮጵያ በየአቅጣጫው የተዥጐረጐረች አገር ነች ካልን በኋላ በግዛቷ ውስጥ የሚገኙት አብዛኞቹ ሕዝቦች ቋንቋቸው የተከለከለ፡ ኃይማኖታቸው የተናቀ፡ ታሪካቸው የተሰረዘ፡ ባጭሩ ጭቁን ህዝቦች. በሙሉ  በድንቁርናና በድርብርብ ጭቆና የተያዙ መሆናቸውን ማመን ያስፈልጋል፡፡

ይህን እውነት ካልተቀበልን አንዳንድ ብሔሮች ይህን ድርብርብ ጭቆና ለመቋቋም ከአማራው ብሔር ቀድመው መደራጀታቸውና መነሳታቸው ሊገባን አይችልም፡፡ ስለዚህ የንቅናቄው መነሻ እነኃይለስላሴ እንደሚሉት የአንዳንድ “እብሪተኞች” ሴራ ወይም “የውጭ እጅ” ያስነሳው እናደርገውና ቁጭ እንላለን፡፡ ከዚያም ደግሞ “በተራማጆች” ትንተና የሚቀርብልን ረቂቅ ቴዎሪ አለ፡፡ አነጋገሩ ቢለዋጥም ግቡ ከላይ ከጠቀስነው ምንም ያህል የማይለይ፡፡

አንዳንድ ጓዶች የብሔሮች ጉዳይ የጊዜው የኢትዮጵያና የአለም ሁኔታ የፈጠረው ትክክለኛ ንቅናቄ ነው የሚለውን አነጋገር ለማፍረስ ይህን ንቅናቄ በጥንቱ በፊውዳሊዝምና /በጉልታዊው ስርአትና/በክፍለ ሃገር መልኩ/በሪጅናሊዝም/ ብቻ ሊወስኑት ይሞክራሉ፡፡ ይህ አነጋገር በጠቅላላው በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ንቅናቄዎች ያላቸውን መልክና ወደፊት ደግሞ ስለአስተዳደጋቸው ያለንን አስተያየት የተሳሳተ ጐዳና ያስይዘዋል፡፡

ከሁሉ አስቀድሞ ዛሬ በኢትዮጵያ የሚታዩትን ብሔራዊ ንቅናቄዎች ሙሉ በሙሉ ከጥንቱ የፊውዳሊዝምና የክፍለ ሃገር ግጭት ጋር ማዋሃድ አይቻልም፡፡ እርግጥ በጥንቱ ሁኔታ ግጭት ሲደረግ የጐጃም ንጉስ ከሸዋ ንጉስ፣ የሰሜኑ ከትግሬ፣ የላስታው ከሸዋ ነበር፡፡ በርግጥ ይህ ከጉልታዊው ስርአት/ ፊውዳሊዝም/ጋር የተቆራኘ ክፍለ ሃገር ከክፍለ ሃገር ንጉስ ከንጉስ ባሉበት ከባላባት የሚጋጭበት ንትርክ ነበር፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ ክፍለ ሃገር ከክፍለ ሃገር እያሉ ሸዋን ከጐጃም፤ ሰሜንን ከሸዋ፤ ሸዋን ከትግሬ፤ ከክፍለ ሃገር ቢያጋጩትም "ከላይ" ያሉት በጋብቻ እየተሳሰሩ የጠበቀ አንድነት እንደነበራቸውና አሁንም በመጠኑ እንዳላቸው ግልጽ ነው፡፡ ይህ ሁሉ እውነት ነው፡፡ ታዲያ ምን ይደረግ፡፡ እኛ እንደምናየው ይህ ሁሉ ዛሬ ከተያዘው ትግል እምብዛም ግንኙነት የለውም፡፡

ያሉትን ብሔራዊ ንቅቃቄዎች በክፍለ ሃገር ግጭት /በሪጂናሊዝም/ ብቻ ወስነው ለማ ቅረብ ሲሞከሩ እነዚህ ጓዶች ኢትዮጵያን ከደገኛው አበሻ ጋር አደባልቀው የዛሬይቱን ኢትዮጵያ በደገኛው አበሻ ወስነው ቁጭ ይላሉ፡፡ ይህንን ስለሚያደርጉ በጠቅላላው የዛሬውን የንጉሰ ነገስቱን ግዛት ግማሽ አካል ማለት እንዳለ ደቡብን፣ የኤርትራንም አንዳንድ ክፍሎች ከትንተናው ረስተዋቸው ያልፋሉ፡፡ እንዳጋጣሚ ሆኖ ደግሞ ብሔራዊ ጭቆናን ለመቋቋም ተደራጅተውና መሳሪያ ይዘው የሚታገሉ ብሔሮች የሚገኙት በነዚህ ክፍሎች መሆኑን እናያለን፡፡ እርግጥ ነው ስለዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሁኔታ ትንተና በሚደረግበት ጊዜ እነዚህ ግዛቶቿ "ከተረሱ" በኢትዮጵያ ያሉት ንቅናቄዎች "ብሔራዊ" መልክ አላቸው ለማለት ያስቸግራል፡፡ ጐጃሜ ከጐንደሬ ቢጣላ የክፍለሃገር ግጭት እንጂ የብሔሮች ግጭት አይደለምና፡፡ እኛ ግን ከዛሬይቱ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ስለምንነሳ ብሔራዊ ንቅናቄ ያሉባቸውን ግዛቶች ሁሉ ከትንተናችን በማስወገድ የክፍለሃገር ግጭት

ያለባቸውን ግዛቶች ብቻ ትንተናችን ውስጥ በማስገባት “ዋናው” የክፍለ ሃገር ግጭት ነው እያልን ትንተናችንን አንዘጋም፡፡

እንዲህ አይነቱ ትንተና ዛሬ በኢትዮጵያ ያሉትን ብሔራዊ ንቅቃሴዎች የሚያናንቅ ተራማጅ ይዞታቸውን የሚስት የወደፊት ታዳጊነታቸው የማያይ የተሳሳተ ቴዎሪ ነው፡፡

ምክንያቱስ ፡፡ምክንያቱም ይህን ቴዎሪ የሚያቀርቡት ጓዶች እንደሚያደርጉት ንቅናቄዎችን በክፍለ ሃገር ወይም በሪጅናል መልካቸው ከወሰንናቸው ጥንት ባላባቶች ከባላባቶች ፤ነገስታት ከነገስታት ከሚያደርጉት ግጭት ለመለየት ፈጽሞ ያዳግተናል፡፡ ስለዚህ የነዚህን ንቅናቄዎች ጸረ-ፊውዳል ይዘት እንዳናየው ያደርገናል፡፡ ግን የዛሬው ልዩ ነው፡፡

በዛሬው ወቅት ጥንት በክፍለ ሃገር ግጭት ዘመን ያልነበረ በሌሎች ብሔሮች ላይ የአማራውን ብሔር ባሕል ለመጫን የሚሞክር መሃከለኛ መንግስት አለ፡፡ ጥንት በክፍለ ሃገር ግጭት ዘመን ያልነበረው የካፒታሊዝም መምጣት ያመጣውና ወደፊትም የሚያመጣው መቀራረብ አለ፡፡ ይኸውም የካፒታሊዝም ወደኢትዮጵያ መግባትና ስር መስደድ የሚፈጥራቸው እና የሚያጋጫቸው ከበርቴዎች/ ካፒታሊስቶች ወይንም ቡርዣዎች/ በብሔሮች መካከል ያለውን ግጭት እያከረሩት እንደሚሄዱ ጥርጥር የለውም፡፡

በዚህ መስመር ለምሳሌ የጊዜው መንግስት ባለስልጣን ከበርቴዎችና ቢሮክራቶች፣ ልዩ ልዩ ተጠቃሚዎች ካፒታሊዝምን ለማስፋፋት የሚያደርጉት መንጠራራት ወደ ጎጃምና ወደቤጌምድር ሳይሆን ወደአዋሽና ወደአዋሳ ማለት ወደ ተጨቆኑት ብሔሮች ግዛት እንደሆነ ለመረዳት አያቅትም፡፡ ይህን ከተረዱ ደግሞ

የነዚሁ ብሔሮች ሕዝብ ጭቆናን ለመቋቋም የሚያደርገው ትግል ወደፊት በኢትዮጵያ የብሔሮችን ጉዳይ ምን ያህል እንደሚያከረው ለመገንዘብ በእውነቱ ምንም ያህል አዳጋች ጉዳይ አይመስለንም፡፡

በዛሬው ወቅት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጭቆናን ለመቋቋምና ንቅናቄዎችን ለመምራት ጥንት በክፍለ ሃገር ግጭት ዘመን ያልነበረ ከባላባቶች ሌላ አዳዲስ ኃይሎች ተፈጥረዋል፡፡ በእነዚህና በሌሎች መአት ሁኔታዎች የተነሳ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የሚደረጉት ንቅናቄዎች በክፍለ ሃገርን እያቆራረጡ የተጣራ ብሔራዊ መልክ ሲይዙ እናያቸዋለን፡፡

ዛሬ በኢትዮጵያ ኦሮሞው ከኦሮሞው አማራው ከአማራው ሲሰለፍ እናያለን፡፡ ወደፊት ደግሞ ይህ ሰልፍ እየተጣራ የሚሄደው በብሔራዊ መልኩ እንጂ በክፍለ ሃገር መልኩ እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ ከእንግዲህ የባሌው ኦሮሞ ከሸዋው ኦሮሞ አይዋጋም፡፡ ከእንግዲህ የትግሉ መነሻ ቃል "ኢልሚ ኦሮሞ ቶኮ" ነው ፡፡ ይህን ሁኔታ መዝኖ ተራማጅ ይዘቱን ከአድሃሪ ይዘቱ ለይቶ መተንተንና ለትግላችን ያለውን አስተዋፅኦ ሆነ እንቅፋትነት ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ይህን እውነት ካልተቀበልን ምንም ነገር ሊገባን አይችልም፡፡ የጐጃምን መነሳት ከባሌ መነሳት እንደሚገባው አንለየውም፡፡ ሁሉቱም ክፍለሃገሮች ናቸውና፡፡ የሸዋው ኦሮሞ ከባሌው፣ ከአርሲው ኦሮሞ ሲተባበር ግራ ይገባናል፡፡ ልዩ ልዩ ክፍለሃገሮች ናቸውና፡፡ ይህን እውነት ካልተቀበልን በተጭቆኑት ብሄሮች ላይ ያለውን ድርብ ድርብርብ ጭቆና ይህም ደግሞ ለትግሉ የሚሰጠውን የመነሻ ሃይል ፈጽሞ ልናየው አንችልም፡፡ ብሔራዊ ንቅናቄን እንንቃቸዋለን፡፡

ስንት ናቸው ዛሬ ከዚህ የተሳሳተ እምነት ተነስተው ይህንን በመሰረታዊ ጉዳዮች ተነሳስቶ የሚታገለውን ሕዝባዊ ንቅናቄ ከነሃይለስላሴ ጋር በጥቅም

የተጋጭኡ ባላባቶችና ከበርቴዎች ብቻ ተገፋፍቶ የተነሳና እነዚሁ ጥቅም ፈላጊዎች እንዳሰኛቸው ቦግ እልም የሚያደርጉት ንቅናቄ የሚመለስላቸው፡፡ ስንቶቹስ ናቸው የጠቅላላውን ጸረ ፊውዳሊና ጸረ-ኢምፔሪያሊስት ይዘት የሚስቱ፡፡ የጠቅላላውን ንቅናቄ ዘላቂነት የሚያቃልሉ፡፡

ለኛ ጥያቄው በጣም ግልጽ ነው፡፡ በመጪው ጊዜ አድሃሪዎች የተበዝባዡችን ትግል ለመቋቋም በሰፊው ሕዝብ መሃከል የፈጠሩትን ጥላቻና አለመግባባት በማባባስና ተጋዳዩን ሕዝብ እርስ በርሱ በማጋጨት የነጻነቱን ትግል ለመከፋፈልና ለማዳከም አይመለሱም፡፡ በተራማጆች በኩል ይህን ቅራኔ ማናናቅ የሰጐዷ ፍልስፍና ይሆናል፡፡ አድሃሪዎች በዚህ ቅራኔ በመጠቀም ፍጅትና ትርምስ ፈጥረው የጋራ የሆነውን የነጻነት ትግል እንዳያሰናክሉት ተራማጆች በሙሉ ተጋግዘው ሰፊው ሕዝብ ከተዘረጋለት ወጥመድ ውስጥ እንዳይገባ መታገል ታሪክ የጣለባቸው ከባድ ሃላፊነት ነው፡፡

አለበለዚያ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ አድሃሪዎች ከሚዘረጉለት ትርምስ ውስጥ እጅና እግሩን ታስሮ፤ ሕሊናው ተመርዞ ከገባ በኋላ ማንኛውም ተበዝባዥ በጠባብ ብሔሩ ተውተብትቦ የመላ ኢትዮጵያን ተበዝባዡች መሰረታዊ አንድነት ዋናውን የበዝባዥና የተበዝባዥ ትንንቅ እውነተኛውን የነጻነት ትግል ረግጦት ሊያልፍ ይችላል፡፡ በዚህም ትርፍ ትርምስ ይበልጡን የሚነዛው መጠላላት፤ ይበልጡን ስር የሚሰደው ቂምና በቀል፤ ይበልጡን የሚመጣው ደም መቃባት መጨረሻው ለማይታይ ረዥም ጊዜ የኢትዮጵያን ተበዝባዡች ባለመግባባትና በደም ግንብ ሊከፋፍላቸው ይችላል፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን በመሰረቱ ጸረ-ፊውዳልና ጸረ-ኢምፔሪያሊስት የሆነው የተበዝባዡች ትግል ሊዘበራርቅና ለጊዜው ሊከሽፍ ይችላል፡፡ ይህ ሁሉ እንዳይሆን ጊዜው የሚጠይቀውን ፖለቲካ በመረዳት ተራማጆች ሁሉ ሃላፊነቱን መቀበል አለባቸው፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ ተበዝባዡች

መካከል ያለውን ቅራኔ ልኩን በመገንዘብ ትግሉን ለማራመድ የማይቆጠብ ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ለዚህም ከሁሉ አስቀድሞ የብሔሮች ጭቆና የወለደውን ንቅናቄ በዛሬው ወቅት ታላቅ አብዮታዊ ይዘት እንዳለው መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ አብዮታዊ ይዘትም ለመላ ኢትዮጵያ ተበዝባዦች ነጻነት መጠቀምን ማወቅ አለብን፡፡

ለ/ የብሔሮች ንቅናቄ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ታላቅ አብዮታዊ ይዘት አለው

ዛሬ በኢትዮጵያ የሚታዩት የብሔሮች ንቅናቄዎች ማንም ይምራቸው ማንም ከስርአቱ የተቆራኘውን የፓለቲካ ጭቆናን ስለሚዋጉ፤ ለሙሉ እኩልነት ስለሚታገሉ፤ በተለይ በደቡብ ግዛቶች ከመሬት ጉዳይ ጋር በጥብቅ የተያያዙ በመሆናቸው መጀመሪያ ላይ ለማንቀሳቀስና ለማደራጀት አስቸጋሪ የሆነውን ገበሬ ለማነሳሳት ስለሚረዱ፤ ሰራተኛውን፤ ንዑስ ከበርቴውንና አገር ወዳድ ከበርቴውን፤ እንዲሁም አገር ወዳድ ባላባቶችን አጠቃለው የሚይዙ ሰፊ ንቅናቄ በመሆናቸው አብዮታዊ ይዘት አላቸው፡፡

ይህ ትግል የተጨቆኑ ብሔሮች በወረራ የተቀሙትን መሬታቸውን ለማስመለስ ብቻ የተነሱበት ሳይሆን፤ በብዙ ዘመናት ውርደትና ጭቆና በራሳቸው ያጡትን እምነትና ኩራት መልሰው ለመጐናጸፍ የታጠቁበት ትግል ነው፡፡ በኢትዮጵያ በእርግጥ እስላሙ ከክርስቲያኑ፤ ኦሮሞው ከአማራው … እኩል የሚሆነው በዚህ ለሙሉ እኩልነት ታጥቆ በተነሳ ትግል የጊዜው ስርአት ተደምስሶ ሲወድቅ ብቻ ነው፡፡ ንቅናቄው ታላቅ አብዮታዊ ይዘት አለው የምንለው ከግቡ ለመድረስ ሲታገል ስርአቱን ያፈራርሰዋል የሚል የጠበቀ እምነት ስላለን ነው፡፡

የአንድ ንቅናቄ አብዮታዊ ይዘት የሚለካው ወቅቱ አካባቢውና ተጨባጩ ሁኔታ እየተመዘነ ነው እንጂ እንዲሁ ዝም ብሎ በባዶ ቦታ አይደለም፡፡ በደፈናው አብዮታዊ የሚባል ነገር የለም፡፡ <u>ስለዚህ የብሔሮች ንቅቃቄን አብዮታዊ ይዘት ስንመዝን ከዛሬይቱ ኢትዮጵያ ተጨባጩ ሁኔታ መነሳት አለብን፡፡</u>

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ መላው ሕዝብ ለዘመናት በተጫነው የጨለማ አገዛዝ የታፈነ ስለሆነ የፖለቲካ ንቃቱ ከመጠን በላይ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የተደራጀ የፖለቲካ ተቃውሞ ልምድ የለውም፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ ዛሬ የጊዜው ስርአት ከኢምፔሪያሊስቶች ገጥሞና በነሱም እየተገዛ ፈጽሞ የማይደፈር መስሎ ይታያል፡፡ በሃገሪቱ የሚነሳውን ማንኛውንም የፖለቲካ ንቅናቄ ለመመዘን ከዚህ እውነት መነሳት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ዝቅተኛ የትግልና የንቃት ደረጃ ተወጥቶ በማንኛውም መልኩ ቢሆን ጭቆናን ለመቋቋም የሚሰነዘርው ማንኛውም የተደራጀ ትግል የስርአቱን መሰረት ለማናጋት ከሚያስፈልገው ናዳ አንድ እንደ ደህና ድንጋይ ሊቆጠር ይገባዋል፡፡ በተለይ ብሔራዊ ንቅናቄዎች ለብዙ ዘመናት ተደላድለው የተቀመጡትን አስካሪ እምነቶችና/ ማለት ዘውዱን የቤተክህነትን የበላይነት/ የመሬት ስሪት፡ የአማራውን የበላይነት.../ ለመቋቋም የሚነሱ እንቅስቃሴዎች በመሆናቸው ማንም ሊንቀው የማይችለውና የማይገባው አብዮታዊ ይዘት አላቸው፡ ፡

አንዳንድ ቦታዎች የነዚህን ንቅናቄዎች አብዮታዊ ይዘት ለማቃለል “ሃይማኖት ላይ የተመሰረቱ ናቸው”፤ “በነገድ ልዩነት ላይ የተመሰረቱ ናቸው” ይሉናል፡፡ ግን እንደዚህ አይነቱ ማወናበጃ ፈጽሞ አያስሸብረንም፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ እስላሙ በሃይማኖት ላይ ተመስርቶ ቢነሳ አስቀድሞ ስርአቱ በሃይማኖት ልዩነት ላይ የተመሰረተ ጭቆና ስለሚያደርግ ነው፡፡ የሃይማኖትን እኩልነት መጠየቅና ለሱም

መታገል ደግሞ የጊዜውን ስርአት አንጠልጥለው ከያዙት የአይዲዮሎጅ/የርእዮተአለም ምሰሶዎች/ማለት የቤተክህነት የበላይነት/ ማናጋት ነው፡፡ ሃይለኛ አብዮታዊ ይዘት አለው፡፡ የምንደግፈውም ይህንን አድልዎ ደምስሶ እኩልነትን ለመፍጠር ቢታገል ነው፡፡ በዚሁ መልክ እነዚህ ንቅናቄዎች "በነገድ ልዩነት" ላይ ተመሰረቱ ቢባልም መልሳችን ያው ነው፡፡ ትግላቸው በአማራው ገዢ መደብ የተቋቋመውን አንዱን "ነገድ" በአንዱ ላይ የሚያደርገውን "የነገድ ልዩነት" ለመቋቋም ነው፡፡ የምንደግፈውም "የነገድ" ጭቆናንና አድልዎን ደምስሶ ሙሉ እኩልነትን ለመመስረት ሲታገል ነው፡፡

አንዳንድ ጓዶች ደግሞ የብሔሮችን ንቅናቄ አብዮታዊ ይዘት ለማቃለል ጸረ-ፊውዳልና ጸረ -ኢምፔሪያሊስት ፕሮግራም የለውም፤ መሪዎቹ ከበርቴዎች እና ንዑስ ከበርቴዎች ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም ባላባቶች ይመሩታል፡፡ ስለዚህ በእነዚህ ታሪክ ባለፉቸው ሃይሎች የሚመራ ንቅናቄ አንደግፍም ይላሉ፡፡ እንደሚመስለን ብዙ ጓዶች የተደበላለቀባቸው እዚህ ላይ ነው፡፡

ነገር ግን እኮ "የብሔሮች ንቅናቄ" ሲባል <u>ምንም ጊዜ ቢሆን አነሳሱ ላይ የሚመራው በከበርቴዎች፤ በንዑስ ከበርቴዎችና እንዲያውም በአንዳንድ አገር ወዳድ ባለባቶች ነው፡፡</u> እርግጥ ነው በዛሬው ወቅት በየትም ያለ ከበርቴ መደብ ሕዝቡን አነሳስቶ እስከ መጨረሻው ድረስ ወደዲሞክራሲ በራሱ  መምራት አይሆንለትም፡፡ ትግሉን እስከመጨረሻ ይቅርና በወጉ መደገፍ እንኳን አይሳካለትም፡፡ እርግጥ ነው በዛሬው ወቅት ማንኛውም ንቅናቄ አብዮታዊ ግቡ የሚደርሰው ከገበሬው ጋር የሚተጋገዘው ሰራተኛው መደብ ሲመራው ብቻ ነው፡፡ በዛሬው ወቅት ዘላቂ አብዮታዊ ሃይል ያለው ለዲሞክራሲ የሚደረገውን ትግል እንኳን ሳያወላውል እስከጨረሻ ሊመራ የሚችለው ሰራተኛው መደብ ብቻ ነው፡፡

ስለዚህ ማንኛውም ንቅናቄ የተራማጆ ችን ሙሉ ድጋፍ የሚያገኘው በተጣራ ጸረ ፊውዳልና ጸረ ኢምፔሪያሊስት ፕሮግራም ስር ተሰልፎ በሰራተኛው መደብ እየተመራ ሲታገል ነው፡፡

ነገር ግን በዛሬው ጭልምልም ባለ ሁኔታ አንድን የተጨቆነ ብሔር አሰልፎ የሚታገል ንቅናቄ ከመጀመሪየው ቁልጭ ያለ ፕሮግራም አላወጣህም ተብሎ አይንህን ለአፈር አይባልም፡፡ ስለአመራሩ ጉዳይ እላይ የሰነዘርነው ሀሳብ ጠቅላላ አቅጣጫ ያሳየናል እንጂ ሁሉንም እውነት/በየጊዜው ሊሆን የሚችለውን ሁሉ/አይወሰንም፡፡ ከበርቴው ትግሉን እስከመጨረሻው አያዘልቀውም ተባለ እንጂ አይጀምረውም አልተባለም፡፡ ሰራተኛው መደብ ትግሉን በመጨረሻው ግቡ ያዘልቀዋል ተባለ እንጂ ከመጀመሪያው አንስቶ ይመራዋል ወይም መምራት አለበት አልተባለም፡፡

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የጭቆናው መልኩና ልኩ የተለያየ ነው፡፡ ስለዚህ ጭቆናን ለመቋቋም የሚነሱት ሃይሎች እጅግ የተሰበጣጠሩ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ላይ በነዚህ ልዩ ልዩ ንቅናቄዎች ውስጥ የሰራተኛው መደብ የተደራጀ ሃይል እጅግ የመነመነ ነው፡፡ ነገር ግን በነዚህ ልዩ ልዩ ሃይሎች በልዩ ልዩ ሁኔታዎች ተገፋፍቶ የተነሳው ትግል ከመሃል አንዳይከሽፍ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ትግሉ የመሪዎቹ ከበርቴዎች ፤ ንዑስ ከበርቴዎችና አንዳንዴም ባላባቶች ጥቅም ሲረካ ትጥቁ እንዳይፈታ ሌላ አብዮታዊ መሪ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ጊዜ ሰራተኛው መደብ በተደራጀ ሃይሉ የትግሉን አርማ ከሚያፈገፍገው ባላባት፤ ከሚርበተበተው ከበርቴ፤ ከሚወላውለው ንዑስ ከበርቴ እጅ መንጥቆ መውሰድና ከገበሬው በመተጋገዝ አብዮቱን ከግብ ማድረስ ታሪካዊ አደራው ነው፡፡

የብሔሮች ንቅናቄ ከዚህ የተለየ የሚከተለው መንገድ የለም፡፡ በያለበት የሚታየው ንቅናቄ አመራር ለጊዜው ከተበዝባዦች እጅ አልገባም፡፡ ነገር ግነ አሁን ባለበት ደረጃና አመራር ያለውን አብዮታዊ ይዘት ፈጽሞ መሳት አይገባንም፡፡ የሃገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ፈጽሞ ሳንመለከት በያለበት የሚደረገው ትግል የደረሰበትን ደረጃ ፈጽሞ ሳንገነዘብ በደፈናው ከበርቴው ዘመኑ አልፎበታል በሚል ፈሊጥ ብንወሰን ለያዝነው ትግል ትልቅ ጉዳት እናመጣለን፡፡ ከዳር ሆነን ከማሽሟጠጥ በስተቀር ዛሬ ከትግሉ የምንደባለቅበትን ምንም አይነት ዘዴ ስለማያሳየን እንደዚህ አይነቱ ቴዎሪ ካለትግል የማይመጣውን ድል ቁጭ ብለን እንድንጠብቅ ያደርገናል፡፡

በበኩላችን ለኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝበ ሙሉ ነጻነት ለሚደረገው ትግል ብሔራዊ ንቅናቄዎች በውስጣቸው ያዘሉት አብዮታዊ ይዘት እስኪያልቅ ድረስ ረዳቶች ናቸው የሚል የጠበቀ እምት አለን፡፡ ነገር ግን ትግሉን የተቀላቀሉት ልዩ ልዩ ሃይሎች በሙሉ እስከመጨረሻ እንደማይዘልቁ እናውቃለን፡፡ ስለዚህ አብዮታዊ ይዘታቸው ሲያከትም አመራሩን ሰራተኛው መደብ በተደራጀ ሃይሉ ተቀብሎ መቋረጥ የማይገባውን አብዮት ወደፊት እንዲያራምደው እንታገላለን፡፡

የተራማጆች ዋና ተግባር ይህንን ትግል ሰብስቦ ቀስበቀስ ጸረፊውዳልና ጸረእምፔሪያሊስት ይዘቱን እያጠሩ ከሰራተኛውና ከገበሬው አመራር ስር ማስገባትና አብዮቱን ከግቡ ማድረስ ነው፡፡

ብሔራዊ ንቅናቄዎች በውስጣቸው እንዲያውም በአመራራቸው ውስጥ ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊዝም የሆነው ፕሮግራም እስከጨረሻው እንዳይዳብር የሚሞክሩ ሃይሎች እንዳሉ አይካድም፡፡ ስለዚህ ተራማጆች እነዚህን እንቅፋቶች ለማስወገድ ሳይታከቱ መታገል አለባቸው፡፡ ነገር ግን እነዚሁ ሃይሎች ዛሬ ትግሉ

ባለበት ደረጃና በጠቅላላው በሃገሪቱ ሁኔታ ሲታዩ ለምንታገልለት ጸረ-ፊውዳልና ጸረ-ኢምፔሪያሊስት ፕሮግራም እንደዋናው እንቅፋት ሆነው ሊታዩ/ሊቆጠሩ ይገባል ወይ፡፡ አይገባም፡፡

ይህንን እውነት የሚቃወሙ ጓዶች ጉዳዩ እንደዚህ ሆኖ አይታያቸውም፡ ስለ "ጸረ-ፊውዳልና ጸረ-ኢምፔሪያሊስት ፕግራም መዳበር " በሚያነሱበት ጊዜ ውሳኔው የሚለው እናቱም አባቱም የሚከተለውን ብቻ ነው፡፡ በንዑስ ከበርቴ ናሽናሊስቶች መደንፋት ሳይወናበዱ.... የኢትዮጵያ ተራማጅ በሙሉ ጸረ-ፊውዳልና ጸረ-ኢምፔሪያሊስት የሆነ ፕሮግራም ማዳበር አለባቸው፡፡ ይህም ማለት ዛሬ በኢትዮጵያ የተያዘው ትግል በደንበኛ ተራማጅ መልኩ እንዳይበለጽግ የሚያግዱት ዋና ጠላቶች በብሔራዊ ስሜት ተገፋፍተው በብሔራዊ ጭቆና ተመርረው የተነሱት ብሔራዊ ንቅናቄዎች ሆነው ቁጭ አሉ ማለት ነው፡፡ ተቃዋሚዎች ጓዶች እዚህ ላይ "የምንቃወመው መሪዎቹን ነው" እያሉ "የማይሞት" መከራከሪያቸውን ይሰነዝሩ ይሆናል፡፡ ግን እስቲ ሰራተኛው መደብ ቀስቅሶ ሰራተኛው መደብ ከመጀመሪያው አንስቶ እየመራ ከግቡ ያደረሰው "ናሽናሊስቶች" አስቀድመው ሳይመሩት ያደገ ብሔራዊ ትግል አንድ ይጥሩልን፡፡

እኛም ብንሆን መቼም "ንዑስ ከበርቴዎች ናሽናሊስቶችን" እልል እያልን አንቀበላቸውም፡፡ ለተራማጅ አላማችንም የሚሰነዝሩትን አደጋ ፈጽሞ አንስተውም ስለዚህ እንታገላቸዋልን፡፡ ነገር ግን በዛሬው ወቅት እነሱን እንደዋና ጠላት በመቁጠር ከነሱ ጋር ባለ ሃይላችን አንተናነቅም፡፡ ምክንያቱም ሌላ ምንም ነገር ሳይሆን እኛና እነሱ የምንተጋገዝባቸው ይበልጥ ሃይለኛ የጋራ ጠላቶች ይበልጥ አጣዳፊ የጋራ ተግባሮች ስላሉብን ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ በኩል እኛ እንደዋና ጠላት አድርገን የምንወስደውና ባለን ሃይል ዛሬ የምንተናነቀው የተጨቋኝ ብሔሮች ብቻ

ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ /ጠላት የሆነው/አድሃሪዎቹ የሚነዙት ትምክህተኛ ብሔራዊ ስሜትን ነው፡፡

## <u>የብሔሮች ትግልና የመደቦች ትግል</u>

ከብሔሮች ትግል ተቀዳሚነት የሚሰጠውና ይበልጥ መሰረታዊ የሆነው የመደቦች ትግል ነው፡፡ በኢትዮጵያ ዋናው ትግል በንጉሰ ነገስቱ ግዛት ውስጥ የሚገኙት ተበዝባዦች በአንድ በኩል፤ በዝባዦች ደግሞ በሌላው በኩል ሆነው የሚሰለፉበት የነጻነት ትግል ነው፡፡ ይህ ማለት ለምሳለ የኤርትራ ተበዝባዥ ሕዝብና የአማራ ተበዝባዥ ምንም አይነት መሰረታዊ የጥቅም ግጭትና ጠብ የላቸውም፡፡ የኤርትራ በዝባዦችና የአማራ በዝባዦች ሌባ ከሌባ ቢጣላ በሰው ገለባ እንደሚባለው በዘረፋው ድርሻ ቢጣሉም ምንም የህል መሰረታዊ ግጭት የላቸውም፡፡

<u>የኢትዮጵያ ተበዝባዦች በሙሉ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን የሚያህሉ የጋራ ጠላቶች አሉባቸው፡፡ የኢትዮጵያ በዝባዦች በሙሉ አብዮቱን ያህል፤ ሕዝቡን ያህል የጋራ ጠላት አለባቸው፡፡ መሰረታዊው እውነት ይህ ነው።</u>

ይህንን ስላልን በሰፊው ተበዝባዥ ሕዝብ መሃከል አለመግባባትና የጊዜ ግጭት የለም ማለታችን አይደለም፡፡ ይህ አለ ነገር ግን ተበዝባዦች ምን ጊዜም ቢሆን የጋራ ጥቅማቸው ከልዩነታቸው ያመዝናል፡፡ ከበዝባዦች ጋር ባላቸው ጠብ አኳያ ሲታይ በእውነቱ በመሃከላቸው ያለው ግጭት በቀላሉ የሚገመት በእርቅና በስምምነት ሊያልቅ የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ ሰፊው ሕዝብና በዝባዦቹ ግን እሳትና ጭድ ናቸው፡፡ ፈጽሞ ሊታረቁ አይችሉም፡፡ ስለዚህ ይህ ግጭት በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ በአንደኛ ደረጃ መታየት ያለበት ዋና ቅራኔ ነው የምንለው ለዚህ ነው፡፡

ይህ ሳይንስን የተመረኮዘ መሰረታዊ እውነት ነው፡፡ ነገር ግን በዝባዦቹ የነሱን አንድነት ለመሸሸግ የሰፊውን ሕዝብ አንድነት ለማፍረስ የማይሞክሩት የላቸውም፡፡ በዘረፋው ጉዳይ እርስ በእርስ በተጋጩ ቁጥር መሳሪያም ያደርጉታል፡፡ በጠቅላላው ለነሱ የሚያመቻቸው ጥላቻ መናናቅ አለመግባባት አለመተማመንና ደም መቃባት ስር ቢሰድና ሰፊው ሕዝብ ቢከፋፈልላቸው ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በዚህ በከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካቸው የተነሳ ሰፊው ሕዝብ ከመጠን በላይ ይከፋፈልና እውነትም መሰረታዊ አንድነቱ ለብዙ ዘመናት ሊድበሰበስና እንዳልነበረ ሆኖ ሊጠፋ ይችላል፡፡ በእንደዚህ አይነት ወቅተ እንደናይጀሪያ አሁን በቅርቡ ደግሞ እንደቡሩንዲ ተበዝባዥ በተበዝባዥ ላይ እየተነሳ ሲተራመስና ሲተላለቅ የመደብ አንድነትና የመደብ ትግል ይረሳል፡፡ በዚህም ልክ ደግሞ የመላ ተበዝባዦች የእውነተኛ ነጻነት ቀን እየራቀ ይሄዳል፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ ካሁኑ ተራማጆች ተገቢ እርምጃዎችን ከልወሰዱ ወደዚህ ትርምስ የምናመራበት አደገኛ ሁኔታ አለ፡፡ ተራማጆች ሁሉ ይህንን እውነት በመረዳት ይህ ከንቱ ትርምስ ታግዶ ትግሉ ወደእውነተኛ የነጻነት ትግል እንዲለወጥ መጣጣር አለባቸው፡፡

አቋማችንን የሚቃወሙ ጓዶች "በደፈናው" ትክክል የሆነውን ዋናው የመደቦች ትግል ነው፡፡ በብሔሮች መሃከል ያለው ቅራኔ የሁለተኛ ደረጃ ቅራኔ ነው፡፡ የብሔሮች ትግል ለመደቦች ትግል መታዘዝ አለበት፤ ለሱም ቅድሚያ መስጠት አለበት" የሚለውን አነጋገር በየውሳኔያቸውና በየጽሁፋቸው ያወርዱልናል፡፡ ሳይንስን የተመረኮዘ የህብረተሰቦች እርምጃ ሕግ አበጥሮ እንደሚያስረዳን የመደቦች ትግል መሰረታዊ ቢሆንም በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅትና በአንድ በተወሰነ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ ያልሆነው የብሔሮች ግጭት የዋናውን ቅራኔ ቦታ ለጊዜው እንደሚይዝ የታወቀ ነው፡፡

በእንደዚህ አይነቱ ጊዜ የተራማጆች ተግባር "ዋናው የመደቦች ትግል ነው" እያሉ አዋጅ ማስነገር አይደለም፡፡ በዚህ ጊዜ የተራማጆች ተግባር አስቀድሞ ይህ ከመጠን በላይ ተጋኖ የሕዝብን መንፈስ አውተብትቦ የያዘው ምንም አይነተ የመደቦች ትግልም ሆነ የትግል ትብብር የሚከለክለውን አለመግባባት ለማስወገድ መታገል ነው፡፡ በበኩላችን የዛሬው ዋና ተግባር ይህ ነው እንላለን፡፡

ዛሬ በኢትዮጵያ ባሉት ብሔሮች መሃከል ለብዙ አመታት የተጠራቀመ በአድሃሪዎች የተነዛ የጥላቻና ያለመግባባት ያለመተማመን መንፈስ አለ፡፡ በአማራው ገዥ መደብ አጥፊ ፕሮፓጋንዳ በመመረዝ የአማራው ሕዝብ የኦሮሞውን፤ የጉራጊውን፤ የትግሬውን፤ የሻንቅላውን ፤ የኤርትራውን ሕዝብ ሁሉ ከመጠን በላይ ይንቃል፡፡ በዚህ አኳያ ደግሞ እነዚህ ሕዝቦች በአማራው ሕዝብ ላይ ትልቅ የጥላቻና የጥርጣሬ ስሜት አላቸው ፡፡ ይህ ሁሉ ተደጋግሞ በኢትዮጵያ ብሔሮች መሃከል ታላላቅ አለመግባባት አለ፡፡ ይህ አለመግባባት በኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታ ከተራ ግጭት አልፎ የዋና ቅራኔ ቦታ በመያዝ ላይ ነው የምንለው የመደቦች ትግል ተገቢ ቦታውን እንዳይዝ ስላፈነውና የኢትዮጵያ ተበዝባዦች አንድነታቸውን አጠንክረው የጋራ ትግላቸውን እንዳያካሂዱ ስለከለከላቸው ነው፡፡

በዚህ መልክ ዛሬ በኢትዮጵያ የታፈነውንና የተድበሰበሰውን የተበዝባዦች አንድነት ተገቢ ቦታውን ሊይዝ የሚችለው ወቅትንና አካባቢን ጨርሶ በሳተ ፈሊጥ እንደአንዳንዶች ጓዶች "የመደብ ትግልን" ቅድሚያ ደጋግመን ብናሰማ አይደለም፡፡ በብሔሮች መሃከል ላለው ግጭት ተገቢ ቦታውን ሰጥተን በቅድሚያ እሱን ለመቀነስ ባለን ሃይል ስንታገል ነው፡፡

ይህን አቋም የሚቃወሙ ጓዶች ባሳለፉት ውሳኔ ላይ የመደብ ትግል ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት ሲያስረዱ እንዲህ ይላሉ፡፡ "በንዑስ ከበርቴ ናሽናሊስትስ ድንፋታ ሳይወናበዱ የኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ … የብሔሮች ጉዳይ ለመደቦች ትግል ቅድሚያ እንዲሰጥ መታገል አለባቸው፡፡" ይህ እኛም የምንስማማበት መሰረተ ሃሳብ/ፕሪንሲፕል ነው፡፡ ነገር ግን ይህ አቋም አንደኛ ነገር ዋናውን ጠላት በሚገባ አይለይም፡፡ እንዲያውም ትምክህተኛ ብሔራዊ ስሜትን የሚያግዝ ነው፡፡ ሁለተኛ ነገር ደግሞ የጊዜውን ተግባር አበጥሮ አያሳይም፡፡ ስለዚህ ለተያዘው ትግላችን ምንም መሳሪያነት የሌለው ትግልን የሚሸሽ አቋም ነው፡፡

ይህ አነጋገር ዋናውን ጠላት ትቶ፤ አድሃሪውን፤ ትምክህተኛ ብሔራዊ ስሜት ትቶ ጭቆናን የሚቃወመውን ብሔራዊ ስሜት ለማጥቃት ይሞክራል፡፡ እርግጥ ነው እዚህም ላይ ትግሉ የተጣራ የመደቦች ትግል መልኩን እንዳይዝ "ለገዛ ብሔሬ ብቻ" እያለ አንድነትን የሚሸሸው ጠባብ ብሔራዊ ስሜት እንቅፋትነት አለው፡፡ ግን አሁንም እንቅፋቱ እሱ ብቻ ነው ወይ፡፡ እንዲያውስ በአሁኑ ወቅት ዋናው እንቅፋት እሱ ነው ወይ፡፡ በፍጹም አይደለም፡፡ ከሱ በኩል እንዲያውም ከሱ ይበልጥ ለመደቦች ትግል ዋናው የጊዜ እንቅፋት የሆነው ገዥው መደብ በአማራው ሕዝብ መንፈስ የሚነዛው ትምክህተኛው ብሔራዊ ስሜት ነው፡፡ የአማራው ሕዘብ የተጨቆኑት ብሔሮች ትግል የሱ ትግል መሆኑ ገብቶት፤ የነሱ ድል የሱ ድል መሆኑን ተገንዝቦት ከወንድሞቹ እንዲደባለቁ ቀስ በቀስ እየተጐተተ ከሚገባበት ከዚህ ወጥመድ እንዲፍታታ ያስፈልጋል፡፡ በኢትዮጵያ ተበዝባዦች በአንድ በኩል በዝባዦች በሌላ በኩል ሆነው የነጻነት ትግል መስመር እንዲይዝ ከተፈለገ አስቀድሞ ትምክህተኛ ብሔራዊ ስሜት በኢትዮጵያ ተራማጆች የተባበረ ትግል መድከም አለበት፡፡

የብሔሮት ትግል በኢትዮጵያ አሁን ከተድበሰበሰበት ሽርኩቻ ወጥቶ ደንበኛ ቦታውን የሚይዘው የብሔሮችን እኩልነት ረግጦ የያዘው የኢትዮጵያ ተበዝባዦች በሙሉ ዋና የጊዜው ጠላት የሆነው ትምክህተኛው ብሄራዊ ስሜት ሲገታ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ይህ እንደ ጸሃይ ብሩህ ሆኖ እየታየ ይህን ትቶ ያኛውን አጥብቀህ ተዋጋ የሚለው አቋም አህያውን ፈርቶ ዳውላውን የሚመታ አቋም ነው፡፡ ለትግላችንም አይረባንም፡፡ እንዲያውም ያደናቅፈናል።

አፍ አውጥቶ አማራው ሕዝብ እስኪነሳ 'እንጠብቅ'፤ ተነሱ ብለን ፊሽካ እስክንነፋ ድረስ "ባለህ እርጋ" ማለት ቢሳነው የተጨቆኑ ብሄሮች ለትግል ቀድመው መነሳታቸውን እንደዋና እንቅፋት አርጎ መቁጠር ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜት ካልሆነ ምን ቃል ይገኝለታል፡፡

በበኩላችን የመደቦች ትግል በተቻለ ፍጥነት በኢትዮጵያ ተቀዳሚ ቦታውን እንዲይዝ የማይቆጠብ ጥረታችንን አናቋርጥም፡፡ ለዚህም የጊዜውን ተግባራችንን ጠቅላላ አዝማሚያ በሚገባ እናውቃለን፡፡ ይኸውም ለጊዜው ዋና የምንለውን የመደቦች ትግል እንቅፋት መዋጋት ነው፡፡ አማራው ህዝብ የተጨቆኑ ብሄሮች ለእኩልነት የሚያደርጉትን ትግል በማደናቀፍ ለጠላቶቹ ለአድሃሪዎቹ መሳሪያ እንዳይሆን፡ <u>በዚህም የራሱን የነፃነት ትግል እንዳያሰናክል</u>፤ አድሃሪዎች ወጥመድ ውስጥ ተወርውሮ እንዳይገባ እናስተምረዋለን፡፡ ይህንንም ስናደርግ የመደቦች ትግል የሚደረጅበትን ዘዴ ማፋጠናችን ነው፡፡ ይህን ስናደርግ ይህንን አቋም እንደሚቃወሙት ጓዶች ስለመደቦች ትግል አዋጅ መናገር ሳይሆን በትግል ለመደቦች ትግል መንገድ መጥረጋችን ነው፡፡

ይህንን አቋማችንን የሚቃወሙ ጓዶች ፈጽሞ ያልተመለከቱት አንድ ነገር አለ፡፡ ኢትዮጵያን የሚያዩዋት 'ከነሱው' ተነስተው ነው፡፡ ሳይንሳዊ የሆነው

የህብረተሰብ እርምጃ ህግ ለነሱ ተገልጦላቸዋልና ሰው ሁሉ የሚገባው መስሎአቸዋል፡፡ ለኢትዮጵያ አብዮት የጊዜውን ተግባር ሲወስኑ፤ መንገዳቸውን ሲቀይሱ መነሻ አድርገው የሚወስዱት የነሱን 'በቴዎሪ መብሰል' ደረጃ እንጂ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ አይደለም፡፡ እኛ ግን በማንኛውም ነገር መነሻ አድርገን የምንወስደው የሃገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ነው፡፡ የኢትዮጵያን አብዮት፤ የጊዜውን ተግባር ስንወስን መንገዳችንን ስንቀይስ የምንነሳው ከኛ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ፤ ከህዝቡ የፖለቲካ ንቃት ደረጃ፣ ከትግሉ.... ወዘተ. እየተነሳን ነው፡፡

ታዲያ ደግሞ የአንድ ህዝብ ፖለቲካዊ ህልና የሚታነጸው ከመጽሀፍ የምናገኘውን 'ቴዎሪ' እንደዳዊት ስንደግምለት አይደለም፡፡ የምንናገረው ሁሉ ሺህ ጊዜ እውነትም ቢሆን ህዝቡ የሚቀበለው የሚያየውን፡ በየእለቱ የሚያጋጥመውን፣ የሚጨበጥለትን እውነት ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ተነስቶ ነው 'ለኛ የምናንበለብለው ቴዎሪ' ከትምህርትና ከትግል በኋላ ሊገባው የሚችለው።

በአሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ "ህዝቡ በሙሉ ነው የተበደለው" የሚሉት አነጋገሮች እውነት ነው፡፡ ግን በቂ አይደለም፡፡ የጊዜው ስርአት የኦሮሞው፡ የጉራጌው፡የትግሬው፡ የኤረርትራው፡ የአማራው ጠላትነት ነው ማለትም ሺህ ጊዜ እውነት ነው፡፡ ግን ይህም በቂ አይደለም፡፡ ይህ እውነት የመላውን የኢትዮጵያ ተበዝባዥ ተቀባይነት አግኝቶ የማይበገር የለውጥ ሞተር የሚሆነው አማራው ተራማጅ የተጨቆኑ ብሄሮችን ትግል በመደገፍ ለትግላቸው አንድነቱን ሲገልጽ፣ የብሄሮችን እኩልነት በማስተማር አድሃሪው ስርአት የሚነዛውን ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜት በድፍረት ሲዋጋ፤ ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ አማራው ህዝብ በበኩሉ

ተነስቶ ይህን ስርአት ለመደምሰስ ከወንድሞቹ ጋር በትግል አብሮ መፈተኑ ሲታይ ነው፡፡

ይህ ደግሞ ጊዜ የሚወስድ ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ትግሉ ከመጀመሪያው ቁልጭ ያለ የመደብ መልኩን ይይዛል ብለን ቅቤ አንጉቱልን አንልም፡፡ በትእግስትና በርጋታ ትክክለኛውን ፖለቲካ እየተከተሉ የመደብ ትግሉን በማገዝ ፈንታ በአንድ ጊዜ ፊሽካ በመንፋት "በኢትዮጵያ ያለህ ተበዝባዥ፣ በኢትዮጵያ ያለህ በዝባዥ በወዲያ" ብሎ ለማሰለፍ መሞከር ጨርሶ የዋህነት ብቻ ሳይሆን የጊዜውን ዋና ተግባር በመሳት ቀስ በቀስ የመደብ መልኩን የሚይዘውን ትግል ማደናቀፍም ይሆናል፡፡

በበኩላችን የጠቀስነውን ትክክለኛ ፖለቲካ /በትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜት ሳንወናበድ/ ከተከተልንና የትግሉን እርምጃ በሚገባ ካገዝነው ትግሉ እየተፋፋመ ሲሄድ የአማራው፡የትግሬው፣ ኦሮሞው፣ የኤርትራው፣ የጉራጌው፣ የወላሞው … ተጋዳይ ህዘብ በትግሉ ውስጥ እየተፈላለገ አንድነቱን ያጠናክራል የሚል የጠበቀ እምነት አለን፡፡ ስለዚህ የብሄራዊ ንቅናቄዎችን አንፈራቸውም፡፡ አናድበስብሳቸውም፡፡ ተራማጆች ሁሉ በተደራጀ ሃይላችን ተቀብለንና አፋፍመን በተቻለ ፍጥነት የመደብ መልካቸውን እንዲዙ ማድረግ የማናወላውልበት አደራችን ነው፡፡

## የትግል አንድነት

በኢትዮጵያ የሚገኙ ተበዝባዦች በሙሉ የጋራ ጠላታቸውን ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ለመደምሰስ የግድ መተጋገዝና መረዳዳት አለባቸው፤ የትግል አንድነት የግድ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ትክክለኛ አቋም ነው፡፡

በበኩላችን ሳናቋርጥ እንታገልለታለን፤ ይህ የትግል አንድነት ሊገኝ የሚችለው ለብዙ ዘመናት በአድሃሪዎቹ የተነዛው የመናናቅ፣ የጥላቻ፣ ያለመግባባት መንፈስ ከሰፊው ህዝብ ህሊና ሲወገዱ ብቻ ነው፡፡

እነዚህም ላይ እንግዲህ ከላይ እንዳልነው የትግል አንድነት በምንልበት ጊዜ ከወቅቱና ከሃገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ተለይቶ ሰማይ ላይ የሚያንዣብብ የቴዎሪ መልስ ብቻውን እምብዛም አይረዳንም፡፡ የረዥም ጊዜ አላማና ተግባር ከጊዜው አላማና ተግባር ተደባልቆ እንዳይቀርብና ለእርምጃ እንቅፋት እንዳይሆን አጥብቆ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡

መጀመሪያ ነገር፣ በአንድ አገር ውስጥ /በተለይ የተለያዩ ብሄሮች ሲኖሩ/ የሚደረገው ጭቆና መልኩም ሆነ ከየብሄሩ የሚያስከትለው መልስ በሺህ በሚቆጠሩ የተለያዩ ነገሮች የሚወሰን ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህም በሃገሪቱ በሙሉ የሚደረገው ጭቆናና የሚከተለውም የፖለቲካ ንቃት በጣም የተለያየና የተበላለጠ መልክ አለው፡፡ ስለዚህ አሁንም ትግሉ ሲጀምር ከዳር እስከዳር በአንዴ ‘ተነሳ’ እየተባለ አይደለም፡፡ ትግሉ አንድ ቦታ ይፋፋማል፡፡ ሌላው ጋር ይዳፈናል፡፡ አንዱ ጋር ይጣደፋል፡፡ ሌላው ጋር ያዘግማል፡፡ አንዱ ጋር በጣም ተራምዷል፡፡ ሌላው ጋር ገና አልታለመም፡፡ በተለያዩ ሁኔታዎች ተጨቁነው ከሚገኙ ተበዝባዦች ጋር ተቀላቅለን ትግል የምናስብ ሰዎች ይቺን ቀላል እውነት ካልተቀበልና የምትሰጠንንም ትምህርት ካልቀሰምን እንዲሁ “የመደብ ትግል” እያልን ስንጠባበቅ ይመሽብናል፡፡

የተግባራችን ሁሉ መነሻ ትግሉ በተበታተነ መልክ መነሳቱን ያምናል፡፡ መቸም የኛን አቋም የሚቃወሙ ጓዶች ይህን የሚስቱት አይመስለንም፡፡ ያቃታቸው የሚመስለን ከዚህ መሠረታዊ እውነት የሚገኘውን ትምህርት መቅሰምና የሚከተለውን ጊዜያዊ ተግባር በሚገባ መወሰን ነው፡፡

ለትግል አንድነት በዚህ ሁኔታ ምን እናድርግ፡፡ ተግባራችንስ ምንድን ነው ሲባል እኛ ወደኋላ የቀረው ይፍጠን እንላለን፡፡ የኛን አቋም የማይቀበሉ ደግሞ አፍ አውጥተው ባይናገሩም የፈጠነው ቀስ ይበል ይላሉ፡፡

ገና “ብሄራዊ ንቅናቄ” ሲባል ጎራዴውን ለመምዘዝ የሚቃጣው ትምክህተኛው አጉል ተራማጅ አቋም ስለዚህ ትግል አንድነት ሲያወራ የሚታየው ያው የፈረደበት “የንኡስ ከበርቴ ናሽናሊስትስ” እንቅፋትነት ብቻ ነው፡፡ ትክክለኛውን አቋማችንን የሚቃወሙት ጓዶች ባወጡት ውሳኔ ላይ እንዲህ ይላሉ፡-

“የኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ በንኡስ ከበርቴ ናሽናሊስትስ ድንፋታ ሳይወናበዱ ... የየብሄሩንና የየክፍለሀገሩን ሰፊ ህዝብ አንድነት መጠበቅና ልዩ ፖለቲካ /ሴክቴሪያን/ የሚከተለውንና አፈንጋጩን መታገል አለባቸው፡፡ … ብዙ ብሄሮችንና ብዙ ክፍለሀገሮችን ጠቅልሎ የሚይዝ አብዮታዊ ድርጅት እንዲቆም መጣር አለባቸው።” ተራማጅ ነኝ ብሎ በነዚህ በተጠቀሱተ አላማዎች የማይስማማ የለም፡፡

ነገር ግን ለዚህ አላማ ሲባል ከማን ጋር ነው በቀድሚያ የምንታገለው። ያልተነሳውን እንቀስቅሰው ወይስ የተነሳውን እንኮንነው፡፡ በተበዝባዦች መሀከል አንድነት እንዳይኖር፣ የተበዝባዦች አብዮታዊ የትግል አንድነት እንዳይቆም /ከየብሄሩ የአንድነት ጠላት ባይጠፋም/ ዛሬ ዋናው እንቅፋት የትኛው ነው፡፡

የእነዚህ ጓዶች አቋም ሃይለኛውን ጊዜያዊ አቋም እየሸሸ ደካማውን ጊዜያዊ ወዳጅ ሲያባርር እዚህም ላይ በትምክህተኛነቱና “በኦፖርቹኒስትነቱ” ይጋለጣል፡፡

እነዚህ ጓዶች ነገሩን ሁሉ አደበላልቀውት ቁጭ ብለዋል፡፡ ለምንፈልገው የትግል አንድነት ዋናው ጊዜያዊ እንቅፋት የተጨቆኑት ብሄሮች መነሳት ሳይሆን የአማራው ተደራጅቶ አለመነሳት መሆኑን መገንዘብ አቅቷቸዋል፡፡ ከሁሉ ይበልጥ ደግሞ አማራው ህዝብ ለገዛ ነፃነቱ ከመነሳት አልፎ በሚመረዝበት ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜት ለአድሃሪዎቹ መሳሪያ ሊሆን እንደሚችል አይታያቸውም፡፡ በዚህም ስሜት እስከተያዘ ድረስ አማራው ቢነሳም ከወንድሞቹ ጋር ሳይሆን በወንድሞቹ ላይ መሆኑን ፈጽሞ ሊያዩት አይችሉም፡፡ ይህንን ሁሉ አደጋ ማየት ስላልቻሉ ደግሞ ዛሬ ለትግል አንድነት የሚደረገው ትንንቅ "የንኡስ ከበርቴ ናሽናሊስቶች" ካዘሉት ንኡስ አደጋ ጋር ብቻ መስሏቸዋል፡፡ እንዲያውም ዋናው ትግል ከሱ ይበልጥ የተበዝባዦች ሁሉ ጠላት ከሆነው ከአድሃሪው ትምክህተኛ ስሜት ጋር መሆኑን መገንዘብ አልሆነላቸውም፡፡

እንደዚህ አይነቱ ቅድሚያን ማደበላለቅ እነዚህን ጓዶች ፈጽሞ የማይለያቸው ምልክታቸው ነው፡፡ ከላይ በመደብ ትግል ያየነውን ያህል ዝቅ ብለን ደግሞ "ስለመገንጠል" መብትና "ስለአንድነት መብት" ስናወራ ደግሞ የባሰውን ዝብርቅርቁን አውጥተውት እናገኛቸዋለን፡፡

በበኩላችን ምንም ጊዜ ጥረታችን የትግል አንድነት እንዲመሰረት ነው፡፡ ከአሁኑ የምንታገለው ለዚሁ አላማ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ የትግል አንድነት ከመጀመሪያው ካልተመሰረተ እያልን ድርቅ በማለት የብሄራዊ ንቅናቄዎች የሰበቡ ለማንቋሸሽ አንሞክርም፡፡ ዋናው ተፈላጊው የትግል አንድነት ተበዝባዦች በሙሉ በአንድነት ተሳስረው በዝባዦችን የሚታገሉበት አንድነት ነው፡፡ ስለዚህ ትግሉ ቀስ በቀስ ከየብሄሩ በተውጣጣ ተራማጆች የተቀናበረና የተደራጀ ጥረት የመደብ ትግሉን እየያዘ ሲሄድ የሚዳብር አንድነት ነው፡፡ ስለዚህ የኛ ተግባር በየወቅቱ የሚጣልብንን አደራ በሚገባ በመረዳትና ተግባራችንን በሚገባ በመፈጸም ይህ ቋሚ

የትግል አንድነት የሚመሰረትበትን መንገድ ለማሰናዳትና የሚመሰረትበትን ጊዜ ለማፋጠን ተግቶ መታገል ነው፡፡

ለዚህ አቋማችን ደግሞ ታሪክ በኛ በኩል ነው፡፡ ታሪክ ደግሞ እንዳሳየው/ዛሬም እንደምናየው/ በዝባዦች ጥቅማቸውን ለመጠበቅ፣ ከህዘብ ለመዳን፣ እንኳን ኩታ ገጠም ሆነው ይቅርና ውቅያኖስም እያቋረጡ ቢሆን የመደብ አንድነታቸውን ይመሰርታሉ፡፡

በኢትዮጵያ የሚደረገው ትግል እየተፋፋመና እያደገ ሲሄድ የየብሄሩ ተበዝባዥ ህዝብ ወላዋይ መሪዎቹን እየጣሰ በማለፍ ዘላቂና ህዝባዊ በሆኑ ግንባር ቀደም ሃይሎች ይተካቸዋል፡፡ በዚህም ጊዜ ከየብሄሩ የተውጣጡትን ወላዋዮችና አድሃሪዎች በያለበት የሚትረፈረፍባቸውንና የሚቀድማቸውን የህዝብ ቅስም ለመስበርና ትግሉን ለመግታት ታርቀው እንደሚተባበሩ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡ የዘመድ ጥል የስጋ ትል ይባላል፡፡ የበዝባዥ ጥል የስጋ ትል ብንለውም ያው ነው፡፡

በትግሉ ውስጥ የበዝባዡ ወገን እየተሳሰረና እየተባበረ ሲሄድ የተበዝባዥም ወገን አንድነቱን እንደብረት እያጠነከረ ወደፊት መግባት አለበት፡፡ ለአድሃሪዎች አመጽ አጸፋው አብዮታዊ የህዝብ አመጽ ነው፡፡ ለአድሃሪዎች ጸረህዝብ አንድነት አጸፋው አብዮታዊ የህዝብ አንድነት ነው፡፡

ጥያቄው ለዚህ ለተበዝባዦች የትግል አንድነት ዛሬ ተግባራችን ምንድን ነው የሚለው ነው፡፡ በኛና የኛን የብሄራዊ ጉዳይ አቋም በሚቃወሙ ጓዶች መሀከል በዚህ ጥያቄ ላይ ያለውን ልዩነት ከፍ ብለን አይተነዋል፡፡

ለዚህ አንድነት መንገድ መጥረግ ማለት ከዛሬው በኢትዮጵያ ተበዝባዦች መሀከል ለዘመናት ሲነዛ ቆይቶ መንፈሳቸውን የመረዘውን ጥላቻና አለመግባባት ማስወገድ ነው፡፡ ተራማጆች ሁሉ ለዚህ መግባባት መስራት አለባቸው፡፡ ለዚህም በአንድ በጠበቀ አብዮታዊ ድርጅት ውስጥ ተሰልፈው የሰፊውን ህዝብ አንድነት ለማጠናከር የተቀናበረ ፖለቲካ ማካሄድ አለባቸው፡፡

ይህም ማለት ከሁሉ አስቀድሞ በትግሉ ውስጥ የአማራው ተራማጅ የሌሎቹን ብሄሮች ትግል መደገፍ ከዚያም የትግላቸውን ፍች ለአማራው ህዝብ ሳይታክቱ ማስረዳትና በበዝባዦች የሚነዛውን ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜት መዋጋት ተግባሩ ነው፡፡ እንደዚሁም ደግሞ የአማራው ሰፊ ህዝብ ተነስቶ ከወንድሞቹ እንዲደባለቅ መጣር አለበት፡፡ በዚህ ጊዜ ብቻ ነው "አማራም ተበዝባዥ አለ" የሚለው የሚኖረውና የሰፊውን ህዝብ ተቀባይነት የሚያገኘው፡፡ እንደዚህ ነው ለትግል አንድነት አንድ ታላቅ መሰረት የሚጣለው፡፡ ለዚህም ዛሬ ተቀዳሚነት የሚሰጠው ተግባር አድሃሪውን ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜት እየተዋጉ ለብሄሮች ሙሉ እኩልነት መታገል ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በትግሉ ውስጥ የተጨቋኙ ብሔሮች ተራማጆች የተለየ አደራ አለባቸው፡፡ በጠቅላላው ህዝቡ ጭቆናን እንዲቋቋም ማነሳሳት፡ ማደራጀት፡ በብሄሩ ውስጥ የመደብ ትግል እያፋፋሙ፡ በዝባዦችን ማገዝ የአማራው ህዝብ ራሱ የተጨቆነ ህዝብ መሆኑን ለተበዝባዦች ሁሉ ማስተማር፡ "ለራሴ ብቻ" እያለ አንድነትን የሚሸሸውን ጠባብ ብሄራዊ ስሜት ሳይታክቱ መዋጋት አለባቸው፡፡ የብሄሩን ትግል ያነሳሱት ከበርቴዎችም ሆኑ ንኡስ ከበርቴዎች በተቻለ ፍጥነት እየታለፉ እንዲሄዱና የህዝብ ትግል እንዲፋፋም ወላዋዮችን ሳይታክቱ ማጋለጥ አለባቸው፡፡ ይህ ትግላቸው ፍሬ ሲሰጥ "ኤርትራዊ በዝባዥ

አለ"፡ "ኦሮሞ በዝባዥ አለ" የሚለው እውነት ተጨባጭ ማመሳከሪያ ያገኛል፡፡ በሰፊው ህዝብ መንፈስ ይቀረጻል፡፡ ለትግል አንድነት ሌላ ታላቅ መሰረት ተጣለ ማለት ነው፡፡ ዛሬ የሰፈነው አድሃሪው ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜት ተዳክሞ እኩልነት እየዳበረ ሲሄድ፣ ተራማጆች በሙሉ ተቀዳሚነት የሚሰጡት ተግባር ጠባብ ብሄራዊ ስሜትን እየተዋጉ ለብሄሮች የትግል አንድነትና መፈቃቀድ መታገል ይሆናል፡፡

## የብሄሮች የገዛ-እድላቸውን መወሰን መብት

ማህበራችን በዚህ በኩል የተቀናበረ ጥንድ ፖለቲካ ይከተላል፡፡ በአንድ በኩል ብሄሮች የገዛ እድላቸውን ለመወሰን ያላቸውን መብት እስከመገንጠልም ድረስ እንዲታወቅ ይታገላል፡፡ ይህ አቋማችን ለብሄሮች ሁሉ ሙሉ እኩልነት የምናደርገው ትግል አካል ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የነገይቱ ኢትዮጵያ ብዙ ብሄሮችን በማፈቃቀድ አቅፋ የያዘች ዲሞክራቲክ አገር እንድትሆን ይታገላል፡፡ ይህ አቋማችን ደግሞ ለሰፊው ህዝብ አንድነት የምናደርገው ትግል አካል ነው፡፡

እንግዲህ ይህ ሲሆን በጣም የምንጠነቀቅበት አንድ ጉዳይ አለ፡፡ የህዝቦችን እኩልነት መጠየቅ፣ የህዝቦችን አንድነት መጠየቅ "በደፈናው" ምንም ተራማጅ አቋም አይደለም፡፡ እነዚህን አላማዎች አድሃሪዎች እንኳን እራሳቸው እናምንባቸዋለን ይላሉ፡፡ በአንድ በኩል "ብሄሮች የገዛ እድላቸውን ለመወሰን፡ መነጠልን የሚጨምር፡ መብት" በሌላ በኩል ደግሞ "ተፈቃቅደው በአንድነት ለመኖር" ያላቸውን መብት ከተቀበሉ በኋላ ተራማጆች ሁሉ ይህ ጥንድ ፖለቲካ የትግላቸው መሳሪያ እንዲሆን እንጂ እርስ በእርሱ እየተጣፋ እንዳያደናቅፋቸው መጠንቀቅ አለባቸው፡፡ አለበለዚያ እንደአድሃሪው፣ እንደትምክህተኛው፣ እንደጠባብ ናሽናሊስቱ በቃላት መጫወትና አይን አውጥቶ ማጭበርበር ይሆናል፡፡

ለተራማጆች ይህ አቋም ተግበስብሶ በጅምላ የሚወረወር አቋም ሊሆን አይችልም፡፡ ነፍስ እንዲዘራበት ከተፈለገ በሁለት አቅጣጫ የተጣራ መልክ እንዲሰጠው ያስፈልጋል፡፡

አንደኛ ትክክለኛው አቋም ለየብሄሩ ግለሰብ ተራማጅ በመልክ በመልኩ የተለየ ተቀዳሚ ተግባሩን ሊያስታውቀው ይገባል፡፡ ይህ "የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ" እንደሚባለው መሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ ትክክለኛ አቋም ለአንድ ተራማጅ ድርጅት በወቅት በወቅቱ እየለየ የጊዜውን ተቀዳሚና አጣዳፊ ተግባር ሊያመለክተው ይገባል፡፡

እናብራራ፡፡ ትክክለኛ አቋም ለየብሄሩ ተራማጅ በመልክ በመልኩ የተለየ ተቀዳሚ ተግባሩን ሊያስታውቀው ይገባል፡፡ ይህም ማለት በዛሬው ወቅት አማራው ተራማጅ ለአማራው ህዝብ የብሄሮችን እኩልነትና ብሄሮች የገዛ እድላቸውን ለመወሰን መገንጠልን የሚጨምር መብት እንዳላቸው ሊያስተምረው ይገባል፡፡ አማራው ተራማጅ "የመገንጠል መብት" እንዲታወቅ መታገል አለበት፡፡ የተጨቋኙ ብሄር ተራማጅ ደግሞ ብሄሩ ውስጥ ያሉትን በዝባዦች ማጋለጥ፣ ከአማራው ህዝብ ጋር ያለውን አንድነት ለማጠንከር፣ በጠቅላላው "የአንድነት መብት" ከስራ ላይ እንዲውል መታገል አለበት፡፡

ተግባሩ እንደዚህ በየመልኩ ካልተከፈለ ጠቅላላ ዝብርቅርቅ ይሆናል፡፡ መጀመሪያ ነገር ብዙ አለመደማመጥን ያስከትላል፡፡ ለኤርትራው ህዝብ አማራው ተራማጅ ሄዶ "ስለአንድነት" ቢሰብክለት አያምርበትም፡፡ ኤርትራው ተራማጅ ለአማራው ሄዶ "ስለመገንጠል መብት" ቢያወራው አይደማመጡም፡፡ አለመግባባት፣ ጥላቻ፣አለመተማመን፣ አለ የሚባለው እኮ ለዋዛ አይደለም፡፡

ግን ደግሞ የባስ አለ፡፡ ተግባሩ በየመልኩ ካልተከፈለ አቋሙ ለአጭበርባሪው “ተራማጅ” ትልቅ የማጭበርበሪያ በር ይከፍትለታል፡፡ ይህ ደግሞ እስካሁን የታየ ነው፡፡ በአንድ በኩል ውሸቱን ለዚህ ጥንድ ፖለቲካ እታገላለሁ እያለ ከአድሃሪው ትምክህተኛ ስሜት ያልተላቀቀው አጉል ተራማጅ አለ፡፡ ይህ “ተራማጅ” የመገንጠልን መብት ለስሙ ቢቀበልም በፕሮፖጋንዳውና በማስተማር ጥረቱ ሁሉ አጥብቆ የሚይዘው “ለአንድነት” የሚደረገውን ትግል ነው፡፡ ስለዚህ ለአማራው ህዝብ የሚያስፈልገው ትምህርት አይደርሰውም ማለት ነው፡፡ በወዲያ በኩል ደግሞ “አለሁ” የሚለው የተጨቋኙ ብሄር “ተራማጅ” ለአንድነት መብት ለይስሙላ ቢታገልም በፕሮፖጋንዳውና በማስተማር ጥረቱ ሁሉ አጥብቆ የሚይዘው በጠባብ ብሄራዊ ስሜት የተበከለውን “የመገንጠል መብቱን” ከግብ ለማድረስ ነው፡፡ ለተጨቋኙ ብሄር ህዝብም የሚያስፈልገው አልደረሰውም ማለት ነው፡፡ በመሀከል ማንኛቸውም የተራማጅ ግዴታቸውን አልፈጸሙም፡፡ የጋራ ትግላቸውን ሳንቲም አልተራመደም፡፡

ሁለተኛ ደግሞ ትክክለኛው አቋም ለተራማጁ ንቅናቄ በወቅት በወቅቱ እየለየ ተቀዳሚና አጣዳፊ ተግባሩን ማመልከት አለበት፡፡ ይህም ማለት ይህን ጥንድ ፖለቲካ በጠቅላላው ካወጁ በኋላ የረዥም ጊዜ አላማውን በዚህ መልኩ ከቀየሱ በኋላ እንደጊዜው እንደአካባቢው፣ እንደትግሉ ደረጃ በመመራት ታክቲክን መቀየስ ያስፈልጋል፡፡ “ብሄሮች የገዛ እድላቸውን ለመወሰን ያላቸው መገንጠልን የሚጨምር መብት” እንዲታወቅ እንታገላለን። “በመፈቃቀድ አንድነት እንዲመሰረት” እንታገላለን ቢባልም ማህበሩ ለሁለቱም መብቶች ሁል ጊዜ በአንድ ሃይል መታገል አይችልም፡፡ ለሁለቱም መብቶች ቢታገልም በትግሉ ውስጥ እንደሁኔታው እያየ አንዱ ላንዱ፤ አንዱ ለሌላው ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡

አለበለዚያ ያው እላይ ያየነው ይሆናል፡፡ ይጣፋል፡፡ ምናልባትም የአድሃሪዎችና የአጉል ተራማጆች መሳሪያነት ከመሆን ቢያመልጥ እንኳን ሸፍንፍን ተልካሻ አቋም ይሆናል፡፡ ለትግል አይመችም፡፡

ለዘላቂ አላማችን የምንታገለው የአማራን ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜትና ለራሴ ብቻ የሚለውን ጠባብ ብሄራዊ ስሜትን ነው፡፡ ነገር ግን በአንድ በተወሰነ ጊዜ ሁለቱንም በአንድ አይን እመለከታለሁ የሚል አቋም ታክቲክና ስትራቴጅን ፈጽሞ የሚያደባልቅ የጊዜውን ዋና ጠላት በሚገባ የማይለይ፣ እሱንም ለመዋጋት በይበልጥ የማይመዝን፣ ዋናውን ትግል የሚሸሽ፣ ወደነፈሰው የሚነፍስ አቋም ነው፡፡

ዋናና ዘላቂ አላማውን ወስኖ ማወጅ ብቻውን የተራማጆች ምልክት አይደለም፡፡ በአንድ በተወሰነ ጊዜም የወቅቱን ዋና አላማ ከጠቅላላው ዘላቂ አላማ ለይቶ መያዝ፤ የበሉ የጠጡትን እየታገሉ እሱን ከግብ ለማድረስ መሞከር ያስፈልጋል፡፡ የትግሉን ዋና ሃይል ወደዋናው ጠላት መልሶ እሱን ማድከም፡ በዚያውም ራስን ማጠንከርና ለተከታዮቹ ጠላቶች በይበልጥ መሰናዳት፣ እነሱንም በተራቸው በዚያው ቆራጥነትና አለማወላወል በመምታት አብዮትን ወደፊት ማራመድ የማንም ተራማጅ ቋሚ ተግባር ነው። ሁሉንም በአንድ እዋጋለሁ የሚለው ተግደርዳሪ አቋም ግን አንዱንም በደንብ አይዋጋም፡፡

እንግዲህ ለኛ ጥያቄው ማን ይቅደም የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ የጊዜው አጣዳፊ ተግባር ምንድን ነው፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ የተናቁና በድርብርብ ጭቆና የተያዙ ብሄሮች ግፍ አስመርሯቸው እኩልነታቸውን ለማስመስከር በተነሱበት ጊዜ አድሃሪው መንግስት ደግሞ "በአንድነት" ስም ኢሰብአዊ አመጹን በሚያወርድባቸው ጊዜ <u>የጋራ ትግላችንን</u> ወደፊት የሚያራምደው ተቀዳሚ ተግባር የትኛው ነው፡፡ በአድሃሪው መንግስት ቦንብና ጥይት በየእለቱ የሚረገጠውንና

የሚሻረውን የብሄሮች እኩልነት ማወጅና እሱም እንዲታወቅ ሳይታከቱ መታገል ነው ወይስ በነዚሁ አጥፊ መሳሪያዎች ተደግፎና በአስካሪ እምነቶች ታጥሮ ለተያዘው "አንድነት" መታገል፡፡ የምንፈልገው "አንድነት" ዘላቂ አላማችን በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ "የእኩዮች አንድነት" መሆኑ ሲታወቅ ተቀዳሚ ተግባራችን የትኛው ነው፡፡ መሰረቱን መጣል ወይስ ልብስ የሚሆነውን ጣራና ግድግዳ አቆማለሁ ብሎ መግደርደር፡፡

በበኩላችን የምንመርጠው መንገድ ግልጽ ነው፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ የብሄሮች ንቅናቄ በሚሰፋፋበት ወቅት በፕሮፖጋንዳችንና በማስተማር ጥረታችን ሁሉ ማህበራችን ተቀዳሚነት የሚሰጠው ብሄሮች እኩልነታቸውንና የገዛ እድላቸውን ለመወሰን ያላቸውን መብት እንዲታወቅላቸው መታገል ነው፡፡

የአማራው ህዝብ አድሃሪዎቹ ሊመግቡት ከሚሞክሩት የበላይነት ስሜት መርዝ እንዲጠበቅ ለእኩልነት መታገል አለብን፡፡ ግን ደግሞ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ በዚያው አኳያ ደግሞ የተጨቆኑ ብሄሮች ህዝቦችም ቢሆኑ ለዘመናት በወረደባቸው አመጽና ጨለማ በራሳቸው ያጡትን እምነትና ሰብአዊ ኩራታቸውን መልሰው እንዲጎናጸፉና በአብዮታዊ አመጽ ወደ እኩልነት እንዲነሱ አመዛኝ ጉልበታችንን ለዚህ አላማ ልናውለው ይገባል፡፡ ዋናው የጊዜው አብዮታዊ ተግባር፣ ዋናው የአንድነታችን መሰረት ይሄው ዛሬ ለእኩልነት የሚደረግ ትግል ብቻ ነው፡፡

ይህን አቋም የሚቃወሙ ጓዶች ነገሩ ሁሉ እንዲህ ሆኖ አይታቸውም፡፡ በመጀመሪያ ነገር ለየብሄሩ ተራማጆች በሚገባ ተቀዳሚ ተግባርን አያከፋፍሉም፡፡ ስለዚህ ውሳኔያቸወን ሲደረድሩ "በኢትዮጵያ ያሉ ተራማጆች በሙሉ" እያሉ ነው የሚያወርዱት፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ለኢትዮጵያ ተበዝባዦች የሚሰጠው ትምህርትም

ሆነ አቀራረቡ አንድ ሊሆን እንደማይችል ከፍ ብለን ለማሳየት ሞክረናል፡፡ አንመለስበትም፡፡

ከዚህ ይበልጥ የነዚህ ጓዶች አቋም ፈጽሞ መስመር የሚስተውና አድሃሪዎቹን ሲያግዝ የሚጋለጠው የጊዜውን ዋና ተግባር ለመቀየስ ሲነሱ ነው፡፡

"በዛሬው ወቅት በኢትዮጵያ ያሉ ተራማጆች ሁሉ በብሄሮች ጉዳይ ጥንድ ተግባር አላቸው" ብለው ደህና ይጀምሩና ዝርዝር ውስጥ ይገባሉ፡፡ ከፍ ብለን እንዳልነው እነዚህን ተግባሮች "እገሌ ይህን፣ እገሌ ያንን" እያሉ አያከፋፍሉም፡፡ እንግዲህ ካሁኑ መሬት ለቅቆ ሰማይ ላይ የሚያንዣብብ አቋም ሆነ ማለት ነው፡፡ ጉዱ የሚፈላው ከዚህ "ጥንድ ተግባር" ውስጥ "ብሄሮች የገዛ እድላቸውን ለመወሰን ያላቸው መገንጠልንም የሚጨምር መብት" እንዲታወቅ መደረግ ያለበትን የአጅቴሽንና የፕሮፖጋንዳ ተግባር አፍ ሞልተው አያነሱትም፡፡ እርግጥ ስለዚህ መብት ያነሳሉ፡፡ እንዲያውም "የመገንልን መብት" እድትታይም እንዳትታይም አድርገው አረፍተ ነገር መሀል ወሸቅ አድርገዋታል፡፡ ለዚያውም ጥንድ ተግባሮችን በሚዘረዝሩባት ቦታ አይደለም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ጥርት ያለ፣ ለትግል የሚመች አቋም የምንጠይቅ ሰዎች ከዚህም አልፈን ደግሞ ብሄሮች በዚህ በኩል ያላቸው መብት እንዲታወቅ በፕሮፖጋንዳና በአጅቴሽን መታገል <u>የጊዜው ዋናና ተቀዳሚ ተግባር ነው</u> ብለን ፍርጥ አድርገን የምንናገር ሰዎች በተራማጆች ስም የሚወጣ ውሳኔ ይህን መብት ይህን ጊዜያዊ ተግባር እንደዚህ ማድበስበሱ ያስደነግጠናል፡፡

እርግጥ ነው የጊዜው ጥንድ ተግባሮች በሚዘረዘሩበት <u>ለወጉ</u> መጀመሪያ ላይ የሚጠቅሰው ተግባር "የኢትዮጵያ ተራማጆች ሁሉ የጊዜውን የንጉስ ነገስቱን

መንግስት ግዛት ወሰኖች መቀበል የለባቸውም'' የሚል ነው፡፡ ይህ ተግባር መጀመሪያ ላይ የተወሰነው ለወጉ ነው ለምንድን ነው፡፡

ይህን ያልንበት ምክንያት መጀመሪያ ነገር ራሱ አቀራረቡ ሲፈሩ ሲቸሩ የሰነዘሩት መሆኑ ያስታውቃል፡፡ ''በወፍ ቋንቋ'' ተናገሩ እንጂ ''የጊዜውን መንግስት ወሰኖች አለመቀበል'' ማለት በተጣራ አማርኛ ሲቀርብ የመገንጠልን መብት መቀበል ነው፡፡ ሁለተኛ ነገር ደግሞ ልብ ላለው ሰው በነዚህ ጓዶች ''የትግል ዘዴ'' ግር የሚል ነገር አለ፡፡ ''የንጉሰ ነገስቱን መንግስት ወሰኖች መቀበል የለብንም'' በሚሉበት ጊዜ /ማለት የመገንጠልን መብት በዘወርዋራ መንገድ በሚቀበሉበት ጊዜ/ በዚህ በኩል ለሰፊው ህዝብ መሰጠት ስላለባቸው ትምህርት፣ ስለፕሮፖጋንዳና ስለአጅቴሽን ሳንቲም አያነሱም፡፡ በዚህ ጉዳይ ዋናው ተፈላጊው ነገር የነሱ ማወቅና አለማወቅ ሆነና ቁጭ አለ ማለት ነው፡፡ ዝቅ ብለው ''አንድነትን አጥብቀህ ያዝ'' ሲሉ ብቻ ነው ''በፕሮፖጋንዳና በአጅቴሽን'' ነጋሪት እያስሙቱ አደባባይ ብቅ የሚሉት፡፡ እንግዲህ በነዚህ ጓዶች አስተያየት በመገንጠል ጉዳይ አስጊው፣ አስፈሪውና አጋፋጩ ፕሮፖጋንዳ መደረጉ ፈጽሞ ትርፉ ድካም ነው ማለት ነው፡፡ እነዚህ ጓዶች ሆን ብለው በየጊዜው ይህን መብት የሚያድበሰብስና በየጊዜው ዋናውን ትግል የሚሸሽ አቋም ስለሚከተሉ ዝቅ ብለን በኤርትራ መገንጠል ጉዳይም ይህን ''ሙያ በልብ ነው'' የሚል ፖለቲካቸውን ይዘው እናገኛቸዋለን፡፡

እንግዲህ እነዚህ ጓዶች <u>ለወጉ</u> ''የመገንጠልን መብት'' ከተራማጅ ተግባር እንደምንም ካወሱ በኋላ <u>ለህዝብ ስለሚሰጠው ትምህርት ሳንቲም ሳያነሱ</u> ''ወደሌላው ተግባር ያልፋሉ፡፡ ይህን ''የተራማጆች ሁሉ ተግባር'' ካወሱ በኋላ በዚህ ተራማጅ ትንፋሻቸው ብቻ አፈራርሰው የጣሉት የመሰላቸውን ''አንድነት''

መልሰው ለመካብና ለመሰብሰብ “በወዲያ በኩል” ሃይልና ጉልበት ጨምረው ብቅ ይላሉ፡፡ ትንተናቸውን በጥሞና ለተከተለ ሁሉ ያስለመዱትን “የንኡስ ከበርቴ ናሽናሊስቶች” እንቅፋትነት እዚህም ላይ ያመጡታል፡፡ ዝቅ ብለውም የነዚህን ጥንድ ተግባሮች ሌላ ይዘት ሲደረድሩ “የኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ… በንኡስ ከበርቴ ናሽናሊስቶች ሳይወናበዱ በፕሮፖጋንዳቸውና በአጅቴሽናቸው የአስዳደር ነጻነት /ናሽናል፣ ሪጅናል ኦቶኖሚን/ አጥብቀው መያዝ አለባቸው ይሉናል፡፡

“ስለመገንጠል ሙብት” ለህዝቡ ሳንቲም ባያስተምሩትም የጊዜው ዋና ተግባር አድርገው ወደሚወስዱት ወደ “አንድነት ሙብት” ሲደርሱ ፕሮፖጋንዳና አጅቴሽኑን በሰፊው ይለቁታል፡፡ እንደዚህ አይነቱ አቋም ተራማጅ ንቅናቄያችን አጥብቆ መያዝ የሚገባውን ተግባር ፈጽሞ የሳተ ነው፡፡ እኩልነትና አንድነት አንጣጣም ብለው በእኩልነትና በነጻነት ስም ብሄሮች እየተነሱ ሲታገሉ፣ በአንድነት ስም ደግሞ እነሃይለስላሴ አድሃሪ አመጻቸውን በህዝቡ ላይ ሲያወርዱት እናያለን፡፡ በዚህ ጊዜ ተረግጦ ለተያዘው የብሄሮች እኩልነት በማድላት በፕሮፖጋንዳና በአጅቴሽን ሰፊ ትምህርት መዘርጋትን ትቶ በነሃይለስላሴ ቦንብ ለሚታገዘው “አንድነት” በይበልጥ ለመታገል የሚግረደር አቋም ሁሉ በህዝብ ትግል የሚያላግጥና ወደ አየለው እያደላ ትግልን የሚሸሽ እብሪተኛና ኦፖርቹኒስት አቋም ነው፡፡

ከዚህ በለይ በጠቅላላው የምንከተለውን የፖለቲካችንን አቅጣጫ አሳይተናል፡፡ በዚህ ላይ አንዳንድ ማብራሪያዎችን መስጠት ተገቢ ይመስለናል።

ከሁሉ አስቀድሞ ይህን “የመገንጠል” ሙብት በማወቃችን አገር ሊከፋፍሉ ተነስተዋል የሚል ማወናበጃ ከያለበት ይሰነዘርብናል፡፡ “ለአንድነት

መብት’’ በመታገላችን ደግሞ አንዳንድ ጠባብ ብሄራዊ ስሜት ያጠቃቸው “ብሄሮች የገዛ እድላቸውን ለመወሰን ያላቸውን መብት’’ አያውቁም ይሉናል፡፡ እዚህ ላይ በዚህ በኩል ሲጻፉ ብዙ ሰዎች የሚጠቅሱትን ምሳሌ መስጠት እንወዳለን፡፡

አንድ ባልና ሚስት ተፈቃቅደው የመጋባት ብቻ ሳይሆን እንቻቻል ሲሉ ደግሞ የመፈታት መብታቸው እንዲታወቅላቸው ይገባል እንላለን፡፡ ይህ የሰው ልጅ ነጻነትና እኩልነት መብት የሚመለከት ጥብቅ ጉዳይ በመሆኑ መብቱ እንዲታወቅ የጋብቻ ሁሉ መሰረትም እንዲሆን ከመታገል አናቆምም፡፡ ነገር ግን “የመፋታት መብት’’ እንዲታወቅ በመታገላችን “ስራ ከመፍታት ልጄን ላፋታት’’ ከሚሉት ወገን ልንቆጠር አይገባም፡፡ የትዳር ጠሮች ተብለን ልንወነጅል አይችልም፡፡ እንዲሁም ለዚህ መብት የምንታገለው ትዳር በእኩልነት በመፈቃቀር በጋራ መፈቃቀድ ላይ እንዲመሰረትና ጽኑ መሰረት እንዲኖረው በማሰብ ነው፡፡

ከዚህ መሰረታዊ እምነታችን ሳንወጣ በአንድ ባልና ሚስት መፋታት ጉዳይ ምክር ብንጠየቅ እንደሁኔታው አይተን የሚበጀውን ተመልክተን “ይፋቱ’’ ወይም ደግሞ “አይፋቱ’’ ልንል እንችላለን፡፡ የቤተሰቡን የጋራ ጥቅም የልጆቹን ሁኔታ የጠቡን መክረር የመቻቻላቸውን እድል፣ ሌሎችም መአት ጉዳዮችን አውጥተን አውርደን ከጨረስን በኋላ ለባልና ለሚስት “አትፋቱ’’ ብለን ልንመክር እንችላለን፡፡ ይህንን ስላደረግን ግን ባልና ሚስቱ ያላቸውን “የመፋታት መብት’’ መርገጣችን አይደለም፡፡ እንደሁኔታው አይተን ደግሞ “ተፋቱ’’ ልንል እንችላለን፡፡ ይህን ስላደረግን ደግሞ በየደረስንበት “የትዳር ጠሮች’’ ልንባል አንችልም፡፡

በሃገር አንድነት ጉዳይ እንዲዚሁ ነው፡፡ ተራማጆች በሙሉ ብሄሮች የገዛ እድላቸውን ለመወሰን መገንጠልንም የሚጨምር መብት እንዳላቸው እንዲታወቅ

በጥብቅ መታገል አለባቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ብሄሮች በመፈቃቀድና በእኩልነት የጠበቀ አንድነት እንዲመሰርቱ መታገል አለባቸው፡፡ የመገንጠል መብትን ማወቃችን መከፋፈልን “ሃይ ሃይ” እያልን ማገዛችን አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በነገይቱ ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያ ብሄሮች ሁሉ በመፈቃቀድና በእኩልነት በአንድነት ይኑሩ ማለታችን ይህን መብት መርገጣችን አይደለም፡፡ እንዲያውም በነገይቱ ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያ የምንታገልላት አንድነት በእኩልነት ላይ የተመሰረተና እያንዳንዱ ብሄር የገዛ እድሉን ለመወሰን ባለው መብት ተጠቅሞ “ይሆነኛል” በሚለው መልክ ከሌሎች ብሄሮች ጋር የሚመሰረተው የእኩዮችና የፈቃደኞች አንድነት ነው፡፡

ይህ ሁሉ ሆኖ አንዱ ብሄር ልገንጠል ያለ እንደሆነስ፡፡ ለምሳሌ “ኤርትራ ትገንጠል” ለሚለው አላማ መልሳችሁ ምንድን ነው እንባል ይሆናል፡፡

ይህ መቼስ እንደሁኔታው እየተጠና የሚመለስ ጥያቄ ነው፡፡ አንድ ብሄር ለመገንጠል መብት አለወይ ለሚለው ጥያቄ መልሳችን ሁልጊዜ አውን መብቱ አለው ነው፡፡ አንድ ብሄር “ይገንጠል ወይ” ለሚለው ጥያቄ ደግሞ ከሁሉ አስቀድሞ መላሾቹ እኛ ሳንሆን የብሄሩ ተበዝባዦቹ ናቸው፡፡ እኛም በየጊዜው በዚህ ተጨባጭ ጥያቄ ላይ ሀሳባችንን ከመስጠትና ለሱ መታገል አናቋርጥም፡፡

በኤርትራ ጉዳይ ከዚህ ጠቅላላ ፖለቲካችን የወጣ መስመር የለንም፡፡ የኤርትራ ህዝብ የገዛ እድሉን ለመወሰን ይታገላል፡፡ በዚህ ጊዜ ተራማጆች ትግሉን መደገፍና የገዛ እድሉን ለመወሰን መገንጠልንም የሚጨምር መብት እንዲታወቅለተ በፕሮፖጋንዳና በአጅቴሽን አጥብቀው መታገል አለባቸው፡፡

እዚህ ላይ መወሳት ያለበት አንድ ዋና ነገር አለ፡፡ ለተጨቆኑ ብሄሮች ተበዝባዥ ህዝብ የምንሰጠው ምክር ተደማጭነት የሚያገኘው አስቀድመን ብሄሮች የገዛ እድላቸውን ለመወሰን ያላቸው በምን አይነት የማይደፈር መብት እንዲታወቅ በሚገባ የታገልን እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ይህን መብት በሚገባ ካወቅን በኋላ፣ እስከመጨረሻ ውጤቱ ተገንዝበን ከተቀበልን በኋላ፣ ጭንቀታችን ለዚህ በጦር ሃይል ታጥሮ ለተያዘው ለጊዜው የእስርቤት አንድነት እንዳይደለ ካሳየን በኋላ፣ ባጭሩ በፕሮፖጋንዳችን ሁሉ ይህ መብት እንዲታወቅ ከታገልን በኋላ ስለአንድነቱ ጉዳይ ምክራችንን ብንሰጥ ያምርብናል፡፡

"ኢትዮጵያ ማለት እኔ ብቻ ነኝ" ብሎ ካከተመው ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜት ለአንዲት ሰከንድ እንኳን ጨርሶ ባልተቆራረጠ አንደበቱ፣ ለአንዲት ሴኮንድ እንኳን ባልተፍታታ ህሊናው ማንም ቢሆን ስለአንድነት ለመስበክ መብት የለውም፡ ፡ በዛሬው ወቅት አስቀድመን በፕሮፖጋንዳና በአጅቴሽን የመገንጠል መብት እንዲታወቅ ሳንታገል "ለአንድነት" እንታገላለን ብንል ከነሃይለስላሴ የምንለይበት ምንም አይነት ፈሊጥ የለም፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ከተቃዋሚዎቹ ጓዶች ጋር ጥብቅ ልዩነት አለን፡፡ የኛ አቋም "የኤርትራ ህዝቦች የራሳቸውን እድል ለመወሰንና ተነጥሎ ነጻ መንግስት እስከማቋቋም ድረስ ያላቸውን መብት" ያውቃል፡፡ ለዚህም የድጋፍ ድምጽ "በየመጽሄቶቹ እንዲሰራጭ እንዲያደርግ" ከዚያም አልፎ "የኤርትራና የኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ ጠላታቸውን ለመደምሰስ በሚያደርጉት ትግል በተግባር ላይ ሊተባበሩ የሚችሉበትን ሁኔታ እንዲያጠና" ባሳለፋቸው ውሳኔዎች አሳሰቦአል፡፡

ትክክለኛው አቋም ይህ ነው፡፡ መጀመሪያ መብቱን ማወቅ ይህ መብትም እንዲታወቅ በፕሮፖጋንዳና በአጅቴሽን መታገል፡፡ ከዚያ ለአንድነት መታገል፡፡ ይህን

አቋም የሚቃወሙ ጓዶች ነገሩን ሁሉ የተገላቢጦሽ ነው የሚያዩት፡፡ ስለኤርትራ መገንጠል ሲያወሩ አስቀድሞ መደረግ ስላለበት የፕሮፖጋንዳና የአጅቴሽን ትግል ሳንቲም አያነሱም፡፡ ራሳቸውም ቢሆኑ ይህን መብት "ለመደገፍ ተሰናድተው የሚገኙት" አስቀድመው የደረደሯቸው ከአሸዋ የሚበዙ ነጥቦች ተሟልተው ከተገኙ በኋላ ነው፡፡ በውሳኔያቸው ላይ የሚሉት እንደዚህ ነው፡=

> "በተበዝባዦቹ አሳሳቢነት መገንጠል ከተጠየቀ በኤርትራ ያለው ንቅናቄ ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊስት ሆኖ በተበዝባዦቹ አመራር ስር ከመጣ፣ ንቅናቄው ከቀሩት የኢትዮጵያ ተበዝባዦች ጋር የትግል አንድነትን አስፈላጊነት ሙሉ በሙሉ ካመነ፣ የመገንጠሉ ተግባር በጠቅላላው ለኤርትራም ሆነ ለኢትዮጵያ ሌላ ክፍለ ሀገሮች የመደብ ትግል የተመቸ ከሆነ ተራማጆቹ ሁሉ በክፍለ ሀገሩ ነጻ መንግስት ሲቋቋም ለመደገፍ ተሰናድተው መገኘት አለባቸው፡፡"

የነዚህ ጓዶች "ተራማጅ ውሳኔ" ያዘላቸውን እርስ በርስ የሚጋጩና የሚጣፉ ሀሳቦች አንባቢ ስራ የፈታ ለት ያሰላሰላቸው ከማለት በስተቀር በዚህ ጥናታችን ውስጥ ልንዘረዝራቸው አንችልም፡፡ ግን የነዚህ ጓዶች አፖርቹኒስት አቋም ምንጊዜም ከዋናው ትግል እንዴት ነጥሏቸው እንደሚቀር ለማሳየት እንወዳለን፡፡ የመገንጠልን መብት ለመደገፍ "ተሰናድተው የሚገኙት" ትግሉ በተበዝባዥ አመራር ስር ከመጣና በትግል አንድነት አስፈላጊነት ሙሉ በሙሉ ካመነ በኋላ ነው ይሉናል፡፡ ይህም ማለት ትምክህተኛ ስሜትም ሆነ "ለኔ ብቻ" የሚል ብሄራዊ ስሜት ተዳክመው ሰፊው ህዝብ የአንድነቱን ጽኑ መሰረት ከጣለና ትግሉ ከፍተኛ ደረጃ ከደረሰ በኋላ ነው ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ጉዱ በብሄሮች መሀከል

መተማመንና አንድነት ዳብሮ ትግሉ እዚህ ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርስ እነዚህ ጓዶች ዛሬ በፕሮፖጋንዳና በአጅቴሽን አስፈላጊውን ጥረት አያደርጉም፡፡ ከዛሬው ትግል በወጉ የሉበትም ማለት ነው፡፡ ነገሳ፡፡ ትግሉ ከዚህ ጓዶቼ "ከሚመኙት" ከፍተኛ ደረጃ ከደረሰ በኋላ ደግሞ የመገንጠል ጥያቄ ቢመጣም ህዝቡ አስቀድሞ ሌሎች ባደረጉት ፕሮፖጋንዳና አጅቴሽን የተሰናዳበት ጉዳይ ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ዛሬ አድፍጠው የሚጠብቁት ጓዶች ነገ "ተሰናድተው" ብቅ ማለታቸው ምን ለመጨመር እንደሆነ እግዚአብሄር ብቻ ይወቅ፡፡ የሆነ ሆኖ ከነገውም ትግል በወጉ የሉበትም ማለት ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ከመጨረሳችን በፊት እነዚህ ጓዶች እንዲህ "የሚረሱትን" የማስተማር ተግባር ዋናነት ለማስተማር እንወዳለን፡፡ የመገንጠል ጉዳይ ሲሆን በነሱ አስተያየት ዋናው ተፈላጊ ጉዳይ "ተራማጆች ተሰናድተው መገኘታቸው" ነው፡፡ ግን እኮ ዋናው ጥያቄ የነሱ መሰናዳት አለመሰናዳት አይደለም፡፡ እኛ ተሰናድተን በሚሊዮን ለሚቆጠረው ህዝብ ማስተማር አለብን፡፡ ይህን ተራማጅ ተግባራችንን በሚገባ ከፈጸምን የመጣ ቢመጣ የምንፈልገው አንድነት ከትርምሱ መበጥ አይመለስም፡፡ ነገር ግን ይህን መብት ተቀብለን ሰፊው ህዝብም እንዲቀበለው ካልታገልን በሄድንበት ብንሄድ የምንፈልገውን አንድነት አድክመነው እናርፋለን፡፡

እንዴት፡፡ ይህ መብት በሰፊው ህዝብ ህሊና እንዲታነጽ አስፈላጊውን ትግል ካደረግን የመጣ ቢመጣ የህዝቡ አንድነት አይሞትም፡፡ አንድ ብሄር በዚህ መብት ተጠቅሞ በቀድሞው ግዛት ውስጥ ለመቆየት ቢፈቅድ ይህ አንድነት በመፈቃቀድና በአንድነት ላይ የተመሰረተ ጽኑ አንድነት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አድሃሪዎቹ በያለበት ለጊዜው አይለው ተቻችሎ መኖር ፈጽሞ አዳጋች ሲሆንና በሁለቱም ወገን በዚህ ጉዳይ የተነሳ የመደቦች ትግል ፈጽሞ ቢታፈን ለተበዝባዦቹ

ሁሉ እውነተኛ የነፃነት ትግል ሲባል ለጊዜውም ቢሆን መለያየቱ ይሻላል፡፡ በዚህም ጊዜ ቢሆን ተራማጆች ይህን መብት አውቀው እንዲታወቅም ታግለዋልና መለያየቱ በሰፊው ህዝብ መሀከል ያለምንም መቃቃር ይፈጸማል፡፡ በሁለቱም ወገን ተራማጆች የቻሉትን ያህል ተግባራቸውን ፈጽመዋልና የመተባበርና የአንድነት መንፈስ ለጊዜው ቢዳፈንም ጨርሶ ከመሞት ይድናል፡፡

ነገር ግን ይህን መብት ካላወቅን /ወይም እንደተቃዋሚዎቹ ጓዶች "ሞያ በልብ ነው" በማለት እኛ "ተሰናድተን" ህዝቡን የማሰናዳቱን ነገር ችላ ካልን/ በየትም በኩል ሲታይ ለሰፊው ህዝብ እውነተኛ አንድነት ምንም አልሰራንም ማለት ነው፡፡ ተጨቋኙ ብሄር እንደምንም ታግሎ ራሱን ነጻ ቢያወጣ ይህን ነጻነቱን ነጥቆ የሚወስደው ከአድሃሪዎቹ ብቻ ሳይሆን ተራማጅ ነን እያሉ ትግላቸውን ካልደገፉት ሰዎችና በትምክህተኛ ስሜት ተመርዞ ከበዝባዦች ተደርቦ ከወጋው ሰፊ ህዝብም ጭምር ነው ማለት ነው፡፡ ይህም መለያየት በሰፊው ህዝብ መሀከል ያለውን መቃቃር ያባብሰዋል እንጂ በምንም አይነት የምንፈልገውን መግባባት አያስገኝም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የተጨቋኙ ብሄር ትግል ለጊዜው ተሸንፎ ብሄሩ ባለበት ግዛት ውስጥ እንደታስረ ቢቆይ ጭቆናው የባሰውን ስለሚቀጥል በሰፊው ህዝብ መሀከል ያለው ጠብና አለመግባባት ከመቼውም እየከረረ ይሄዳል፡፡

## <u>መደምደሚያ</u>

ከላይ የጠቀስናቸው ልዩነቶች ተጠራቅመው እኛንና ተቃዋሚዎቹን ጓዶች በጠቅላላው በኢትዮጵያ አብዮት ሁለት የተለያዩ ታክቲኮችን እንድንከተል ያደርጉናል፡፡

የኛ አቋም ከትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜትም ሆነ ከጠባብ ብሄራዊ ስሜት ፈጽሞ የተላቀቀ አቋም ነው፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ ካለው ተጨባጭ ሁኔታና ከዝቅተኛው የትግል ደረጃ ይነሳል፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ በልዩ ልዩ ብሄሮች መሀከል ጥላቻና አለመግባባት አለ፡፡ ይህም ቅራኔ በመጭው ጊዜ እየከረረ ሊሄድ እንደሚችል ያምናል፡፡ እንዲያውም ተራማጆች ሁሉ በየበኩላቸው ተግባራቸውን በሚገባ ካልፈጸሙ የኢትዮጵያ ተበዝባዦች በሙሉ ለነጻነት ትግላቸው ሊያውሉት የሚገባውን ሃይል አሰቃቂ በሆነ የእርስ በእርስ ትርምስ ሊያባክኑት የሚችሉበት አደጋ አለ ብለን እናምናለን፡፡ አቋማችን ከዚህ እውነት ተነስቶ የከረረው ቅራኔ የሚለሳለስበትን፣ የመነመነው አለመግባባት የሚዳብርበትን ዘዴ ያመለክታል፡፡ አቋማችን የተያዘውን ትግል ወደፊት የሚያራምድ፣ የተጋዳዩን ሰፊ ህዝብ የትግል አንድነት የሚያረጋግጥ፣ ነገ ደግሞ በኢትዮጵያ የሚገኙት ብሄሮች በመግባባትና በአንድነት የሚኖሩበትን መንገድ የሚጠርግ አቋም ነው፡፡ ለዚህም ሁሉ በደፈናው የሚወረወር የቴዎሪ መልስ ብቻውን ምንም ዋጋ እንደሌለው በመገንዘብ የጊዜውን ዋና ጠላት በማመልከት የጊዜውን ዋና ተግባር በመወሰን ዛሬ በመላ ኢትዮጵያ ከሚደረገው ትግል በግንባር ቀደምነት የምንደባለቅበትን ዘዴ አበጥሮ ያሳያል።

ይህን አቋም የሚቃወሙት ጓዶች ከአጠቃላይ ቴዎሪ ወጥተው ኢትዮጵያን ማሰላሰሉ ፈጽሞ አልተሳካላቸውም፡፡ ለዚህ ነው ለምሳሌ “ዋናው የመደቦች ትግል ነው” በሚል በደፈናው እውነት ከሆነ አነጋገር ተነስተው ዛሬ በኢትዮጵያ ብሄሮች መሀከል ያለውን ግጭት የሚንቁት፡፡ ለዚህ ነው ለምሳሌ ይህ ቅራኔ በጊዜ ካልተፈታ “የመደቦች ትግል” መጨረሻው ለማይታይ ረዥም ጊዜ በእርስ በእርስ ትርምስ ተውጦ ሊቀር እንደሚችል እኛ የሚታየን አደጋ ለነሱ የማይታያቸው፡፡

እነዚህ ጓዶች ከአጠቃላይ ተግባርና ከዘላቂ ግብ ማወጅ ወጥተው ዛሬው ባለው ሁኔታ የጊዜውን ዋና ተግባር በሚገባ መወሰን ተስኗቸዋል፡፡ ለዚህ ነው ለምሳሌ ለትግል አንድነትም ሆነ በጠቅላላው ለትግሉ እድገት በሚያደርጉት ጥረት ዋናውን እንቅፋት ረስተው “ንኡስ ከበርቴ ናሽናሊስቶችን” እንደዋና ጠላት ሲያሳድዱ ከትምክህተኞችና “ከኦፖርቹኒስቶች” ጋር ተደባልቀው የሚጋለጡት፡፡ ለዚህ ነው ለምሳሌ ለእኩልነትም ለአንድነትም እንዋጋለን ቢሉም የጊዜውን ዋና ግብ መወሰን አቅቷቸው ከሁለት ያጣ ጎመን የሆኑት፡፡

የነዚህ ጓዶች አቋም በየሰበቡ ብሄራዊ ንቅናቄዎችን የሚንቅ፣ ትምክህተኛና ከአየለው ጋር የሚያይል፣ ትግልን የሚሸሽ “ኦፖርቾኒስት” አቋም ነው፡፡ ስለዚህም በዛሬው ትግል ሰፊው ህዝብ፣ ንኡስ ከበርቴው፣ አገር ወዳድ ከበርቴውና እንዲሁም አንዳንድ ባላባቱ ሁሉ ተግበስብሶ ከሚዋጋበት ከዝቅተኛው የትግል ደረጃ በግንባር ቀደምነት ተደባልቀን ትግሉን ከፍ የምናደርግበትን ዘዴ አያሳይም፡፡ ስለዚህ ከዳር ቆመው ከሚሽሟጠጥ በስተቀር ምንም የረባ የትግል መስመር ስለሌላቸው በውሳኔያቸው መጨረሻ ወደማያመልጡበት መደምደሚያ ይወስዱናል፡፡ በመጨረሻም” ይሉናል እነዚህ ጓዶች ውሳኔያቸው መደምደሚያ ላይ “በመጨረሻም ተራማጅ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ስለብሄሮች ጉዳይ…ጥናታቸውን መቀጠል አለባቸው”፡፡

እኛስ፡፡ የኛ አቋም እርግጥ ይህንን ዝቅተና የትግል ደረጃ “እልል” እያለ አይቀበለውም፡፡ ነገር ግን የሀገሪቱ ታሪካዊ ሁኔታ ያፈራው ነገር በመሆኑ ከሰው ለመነሳት እንደ አንድ ታሪካዊ የትግል ደረጃ አድርገን እንቀበለዋለን፡፡ ለኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ነጻነት፣ እኩልነት፡ አንድነትና፡ ብልጽግና የምንታገለው የግድ ከዚህ ዝቅተኛ ደረጃ በግንባር ቀደምነት ተዋህደን መሆኑ ይገባል፡፡ ስለዚህ እነሱ “ይጠና”

በሚሉበት ጊዜ የኛ አቋም በኢትዮጵያ ካሉት ብሄራዊ ንቅናቄዎች ጋር ለጋራ ትግላችን የምንተባበርበትን ዘዴ ያሳያል፡፡

የማህበራችን አቋም ለበሰበሰው ስርአት አደገኛነቱ፣ ለኢትዮጵያ ተበዝባዦች ትግል ደጋፊነቱ እዚህ ላይ ነው፡፡ "እኩልነት"፣ "አንድነት"፡ "የመደብ ትግል"፡ ወዘተ. እያለ መሪ ቃላትን ከመወርወር አልፎ ለነዚህ አላማዎች በጥብቅ ይታገላል፡፡ እንደዚህ ነው ጭቆና በየመልኩ የሰፈረባት ኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ከብረት የጠነከረ አንድቱን መስርቶ በአብዮታዊ አመጽ በዝባዦችን እንደጎርፍ የሚያጥለቀልቃቸው፡፡ እንደዚህ ነው የተደራጀው የህዝብ ትግል አገሪቱን የሚያጥባት፡፡ ለዚህ ነው አድሃሪዎችን ሁሉ የማህበራችን አቋም እንደዚህ ያስቆጣቸው፡፡

ንጋት አምዴ